# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበረሰብ ሳይንስእናስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል

"ተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድ ከልበ-ወለድ አላባውያን አንፃር

በ

ሰብለወርቅ አጉማሴ

ነሐሴ/20013 ዓ.ም

# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

"ተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድ ከልበ-ወለድ አላባውያን አንፃር

በ

ሰብለወርቅ አጉማሴ

የጥናቱ አማካሪ

መምህር ተመስገን ሽታይ

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለ ቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር አፍ አርትስ

ድግሪ ማሟያ ነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ነሐሴ/2001ዓ.ም

# የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማመከሪያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም.....ፊርማ.....

ይህ በተማሪ ሰብለወርቅ አጉማሴ"ተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድ ከልበ-ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያ ጥንታዊ ፅሑፍ  የዩኒቨርስቲውን ጥራት ደረጃ ያሚላ እና ለቴአተር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጣል።

ፈታኝ1 ፊርማ

..... .....

ፈታኝ2 ፊርማ

..... .....

ቀን.....

# ምስጋና

በመጀምሪያ ኤልሻዳይ ለሆነው ለድንግል ማርያም ልጅ አማኑኤል በእድሜ ዘመኔ ሁሉ ስላደረገልኝ ነገር እስከ እናቱ ይመስገንልኝ።በመቀጠልም እንደሻማ ቀልጣ ለበራችልኝ እራሷን አሳንሳ እኔን ከፍ ላደረገችኝ ውዷእናቴለየሰራሽወሌ፤ከንኔለማይለዩኝ ጭንቀቴጥንቀታቸውለሆነው ወንድሞቼ ለአብርሀም እና ሙሉጌታአጉማሴ ፤ከንኔ ሆኖ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ለሚያሚላልኝ አባቴ አጉማሴ ጋሽ ምስጋናየ ቃላት የለውም።በመጨረሻም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በምሰራበት ጊዜከንኔ ሆኖ ሞያዊ ምክሮችን ሳይሰስት ለለገሰኝ ለመምህር ተመስገን ሽታየ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሰው።

# አበርክቶ

ይህ ጥናታዊፅሁፍ ትምህርትን ጀምራ ላልጨረሰችው የእርሷን አለምትታ ለልጆቿ ለኖረችው ውድ እናቴ የሰራሽ ወሌ ይሁንልኝ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ከረጅምልበ-ወለድ አላባውያን አንፃር ምን እንደሚመስል እና አላባውያኑ በልበ-ወለዱ ውስጥ መገለፃቼውን በትንታኔ መልክ በመፈተሽ ያሳያል።ተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ሁሉንም የልበ-ወለድ አላባውያን የተጠቀመ ሲሆን እያንዳድጅንዳቸውን የልበ-ወለድ አላባውያን አጥኝዋ በመረጃ አስደግፋ በስፋት እናበጥልቀት ተነትናለች።

# ማዉጫ


የአማካሪው ማረጋገጫ ..... I

ምስጋና ..... II

አበርክቶ ..... III

አጠቃሎ ..... IV

ምዕራፍ አንድ ..... 1

1. መግቢያ ..... 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ..... 2

1.2. የጥናቱ አላማ ..... 2

1.2.1. የጥናቱ አብይ አላማ ..... 2

1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ ..... 2

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3

1.4. የጥናቱ መጠነ-ርዕይ ..... 3

1.5. የጥናቱ ዘዴ ..... 4

1.5.1.የጥናቱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ..... 4

1.5.1.1. የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ..... 5

1.6. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ..... 5

1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ..... 6

መዕራፍ ሁለት ..... 7

2.1. የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፎች ቅኝት ..... 7

2.2.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ..... 8

2.2.1. የ ስነ ጽሁፍ ምንነት ..... 8

2.3. የ ልብ-ወለድ ምንነት ..... 9

2.3.2. ረጅም ልብ-ወለድ ..... 10

2.3.1. አጭር ልብ-ወልድ ..... 11

2.4. የልብ-ወለድ አላባዊያን ..... 11
2.4.1. ታሪክ ..... 12
2.4.2. ትልም ..... 12
2.4.3. ገጸ-ባህርያት ..... 13
2.4.3.1. ፊርጀብዙ ገጸ-ባህርያት ..... 14
2.4.3.2. ፊርጀ አንድ ገፀባሕርያት ..... 14
2.4.4. ግጭት ..... 15
1.4.4.1. የግጭት አይናቶች ..... 16
2.4.4.2. ሰው ከሰው ጋር ያለው ግጭት ..... 16
2.4.4.3. ሰው ከራስጋር የሚያደርገው ግጭት ..... 17
2.4.4.4. ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የሚያደርገው ግጭት ..... 18
2.4.4.5. ሰው ከተፈጥሮ ጋር የመሚያደርገው ግጭት ..... 18
2.4.5. መቼት ..... 20
2.4.5.1. የመቼት አይነቶች ..... 20
2.4.5.2. አጠቃላይ መቼት ..... 21
2.4.5.3. ውስን መቼት ..... 21
2.4.6. ጭብጥ ..... 22
2.4.6.1. አካባቢያዊ ጭብጥ ..... 23
2.4.6.2. ሁለንተናዊ ጭብጥ ..... 23
2.4.7. አንፃር ..... 24
2.4.7.1. ሁሉን አዎቅ አንፃር ..... 25
2.4.7.2. ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር ..... 25
2.4.7.3. አንደኛ መደብ አንፃር ..... 26
2.4.7.4. ተውኔታዊ አንፃር ..... 26
3.1. የተልሚድ እረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ..... 27

3.2. "የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ከልበ- ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና ..... 29
3.2.1. የተልሚድ ልበ-ወለድ ታሪክ ..... 29
3.2.2. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ትልም ..... 29
3.2.3. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ገፀ-ፀባህርያት አሰሳል ..... 30
3.2.3.1. የተልሚድ አካላዊ አሰሳል ..... 30
3.2.3.2. የተልሚድ ማህበራዊ አሰሳል ..... 31
3.2.3.3. የተልሚድ ስነ-ልቦናዊ አሰሳል ..... 31
3.2.3.4. የተልሚድ ሞራላዊ አሰሳል ..... 32
3.2.3.5. የዝንመሪቅ አካላዊ አሰሳል ..... 33
3.2.3.6.የዝንመሪቅ ማህበራዊ አሰሳል ..... 33
3.2.3.7.ዝንመሪቅ ስነ-ልቦናዊ አሰሳል ..... 34
3.2.3.8. ዝንመሪቅ ሞራላዊ አሰሳል ..... 34
3.2.3.9. የፀዳይ አካላዊ አሰሳል ..... 35
3.2.3.10.የፀዳይ ማህበራዊ አሰሳል ..... 36
3.2.3.11. የፀዳይ ስነ-ልቦናዊ አሰሳል ..... 36
3.2.3.12. የፀደይ ሞራላዊ አሰሳል ..... 37
3.2.3.13. ብሩክታዊት አካላዊ አሳሳል ..... 37
3.2.3.14. የብሩክታዊት ማህበራዊ ..... 37
3.2.3.15. የብሩክታዊ ስነ-ልቦናዊ አሳሳል ..... 38
3.2.3.16. የብሩክታዊት ሞራላዊ አሳሳል ..... 39
3.2.3.17. የዝንመሪቅ ጥበቃ አካላዊ አሳሳል ..... 39
3.2.3.18. የዝንመሪቅ ጥበቃ ማህበራዊ አሳሳል ..... 39
3.2.3.19. የዝንመራቅ ጥበቃ ሞራላዊ አሳሳል ..... 40
3.2.3.20. የብጡል አካላዊ አሳሳል ..... 41
3.2.3.21. የብጡል ማህበራዊ አሳሳል ..... 41

3.2.3.22. የብጡል ስነ -ልቦናዊ አሳሳል ..... 41
3.2.3.23. የብጡል ሞራላዊ አሳሳል ..... 42
3.2.3.24. የወይዘሮ ስናይት አካላዊ አሳሳል ..... 42
3.2.3.25. የወይዘሮ ስናይት ማህብራዊ አሳሳል ..... 42
3.2.3.26. የወይዘሮ ስናይት ስነ-ልቦናዊ አሳሳል ..... 43
3.2.3.27. የወይዘሮ ስናይት ሞራላዊ አሳሳል ..... 43
3.2.4 " የተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ ግጭት ..... 44
3.2.5. የ"ተልሚድ" ረጅም ልበ-ወለድ መቼት ..... 45
3.2.5.ነ. የ"ተልሚ"ረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ የቦታመቸት ..... 45
3.2.5.3. "የተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ የጊዜ መቼት ..... 48
3.2.5.4. "የተልሚድ" ረጅም ልበ-ወለድ ውስን የጊዜ መቸት ..... 48
3.2.5.5."የተልሚድ" ረጅም ልበ-ወለድ ማህበራዊ እውነታ ..... 49
3.2.6. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ጭብጥ ..... 49
3.2.7. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ አንፃር ..... 51
ምዕራፍ አራት ..... 52
4.ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃስቦች ..... 52
4.ነ. ማጠቃለያ ..... 52
4.2. የመፍትሄ ሐሳብ ..... 53
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ..... 1
ዋቢ መፅሐፍት ..... 1

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ስነ-ፅሁፍ የሰው ልጅ ገጠመኝ፣ፍላጎትና የህይወት ልዩ ልዩ ገፅታወች በቋንቋ አማካኝነት በቃልም በፁህፍም የሚያቀርብ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው። ስነፁህፍን ዘሪሁን አስፋው "የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን" በተሰኘው መፅሀፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል። ስነ-ፅሁፍ በተለያዩ ቅርፆች አማካኝነት የሚከሰት በሰዎች ለሰዎች የሚቀርብ የገጠመኝ ማንፀባረቂያ እውነትን በአንድ አጣምሮ የሚይዝ ህልውናው በቃልም በፅሁፍም የሆነ የፈጠራ ስራ ነው።(2005፣1) እንደ ዘሪሁን አስፋው ገለፃ ስነ-ፅሁፍ ማለት በውስጡ ተውኔትን፣ስነቃልን፣ረጅምና አጭር ልብ-ወለድን ያጠቃልላል። ከነዚህ የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች መካከል በዋነኝነት የምናገኘው ልብ-ወለድ ነው። ልብ-ወለድ ማለት በእውኑ አለም የሚንቀሳቀሱን ፍጥረታት በተለያዩ የሰው ልጆችን ማህበራዊ፣ምጣኔ ሀብታዊ ፖለቲካዊ ህይወትን ስዕላዊ በሆነ መንገድ በቋንቋ አማካኝነት የምናንፀባርቅበት ዘዴ ነው። ይህንን ሀሳብ ዘሪሁን አስፋው " የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን" በተሰኘው መፅሀፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

"ልብ-ወለድ" የግለሰባዊና ማህበረሰባዊ ህይወታችን ልዩ ልዩ ልዩ ገፅታዎች የሚያንፀባርቅበት በቃላት አማካኝነት የሚገለፅ ምዕናባዊ ምስል ያለው ነው። ልብ-ወለድ ከስነ-ፅሁፍ ባህሪዎች አንፃር ረዥምና አጭር ልብ-ወለድ በመባል በሁለት ይከፈላሉ።

አጭር ልብ-ወለድ ሰብሰብ ያሉ ወይም ሶስትንም የአጭር ልብ-ወለድባህሪያትን ማለትም ቁጥብነት፣ ጥድፊያ፣ነጠላ ውጤትን ያሟላ፣ፍጥነት ጎልቶ የሚታይበት፣አንድ ብቻ የትኩረት ነጥብ ያለው፣ በአጭር ታሪክ የተዋቀረ ነው። ረጅም ልብ-ወለድ እርስበርሱ የሚደጋገፍ ከአንድ በላይ ታሪኮች የሚይዝ፤በርካታ ገፀ-ባህሪያትን የሚያሳትፍ መቸቱ እጅግ ሰፊና ታሪኩ እያዘገመ የሚሄድ የልብ-ወለድ አይነት ነው።(2005፣ 152)

ልብ-ወለድ ማለት በደራሲው ምዕናብ የሚፈጠር የደራሲው የፈጠራ ስራ ነው። ልብ-ወለድ ከፅሁፋዊ ስነ-ፅሁፍ የሚመደብ በዝርው የሚቀርብ የሰውን ልጅ ልዩ ልዩ ገጠመኞችን እና በምዕናብ የሚፈጠሩ

ታሪኮችን ጥበባዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርብ የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ነው። ልብ-ወለድ በሚይዘው የታሪክ መዋቅር አጭርና ረጅም ልብ-ወለድ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። አጭር ልብ-ወለድ አንድ ብቻ ታሪክ ያለው፣በፍጥነት ተጀምሮ በፍጥነት የሚያልቅ ትንሽ ገፀ-ባህሪያትን የሚያሳትፍ የልብ-ወለድ አይነት ነው። ረጅም ልብ-ወለድ ሰፊ ታሪኮችን ከውልደት እስከ ሞት የሚተርክ ፣ብዙ ገፀ-ባህሪያትን የሚያሳትፍ የልብ-ወለድ አይነት ነው። አንድ ልብ-ወለድ በሚፃፍበት ጊዜ በሰባት አይነት የልብ-ወለድ አላባዊያን መዋቅር አለበት። የልብ-ወለድ አላባዊያን የሚባሉትም ታሪክ፣ትልም፣መቼት፣ገፀ-ባህሪያት፣ግጭት፣ጭብጥና አንፃር ናቸው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም ከነዚህ የስነ-ፅሁፍ አይነቶች መካከል"ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድን ከረጅም ልብ ወለድ አላባውያንአንፃር አጥኝዋ ትተነትናለች።

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

አጥኝዋ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ያነሳሳት ዋነኛ ምክንያት የልብ-ወለድ አላባዊያን በልብ-ወለድ ውስጥ ያላቸውን አስተዋፅኦ ለመመርመር እና "በተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ ውስጥ ያሉትን አላባዊያን በምን መልኩ እንንደተገለፀ ለመተንተን በመፈለጓ ነው።

### 1.2. የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በውስጡ አብይና ንዑሳን አላማዎችን አካቶ የያዘ ነው።

### 1.2.1. የጥናቱ አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ ተልሚድ በተሰኘው ረጅም ልብ-ወለድ ውስጥ የልብ-ወለድ አላባዊያንን አጠቃቀም መፈተሸና መተንተን ላይ ትኩረቱን ያደርገ ነው።

### 1.2.2. የጥናቱ ንዑስ አላማ

- ስለ ስነ-ፅሁፍ ምንነት ማሳወቅ

- የረጅም ልብ-ወለድን ምንነት ማሳወቅ

- ስለ"ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ ትንታኔ መስጠት

- በ"ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ የትኞቹ የልብ-ወለድ አላባዊያን እንደተገለፁና ያላቸውን ፋይዳ

ማብራራት።

### 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

- ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ስለ"ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ አላባዊያን ምንነትና በልብ-ወለዱ ዉስጥ እንዴት እንደተገለፀ ግንዛቤ ይሰጣል።

- በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ርዕስ ዙሪያ ተመሳሳይ ይዘት ላላቸው ጥናታዊ ፁህፎች እንደ ምንጭ በመሆን ይጠቅማል።

- ለባችለር አፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያነት ያገለግላል።

### 1.4. የጥናቱ መጠነ-ርዕይ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መጠነ-ርዕይ በደራሲ ይስማከ ወርቁ በ2002ዓ.ም የተደረሰ ለሁለተኛ እትም በ2005ዓ.ም ለህትመት በበቃው "ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ ከልብ-ወለድ አላባዊያን አንፃር መተንተን ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን በአራት ምዕራፎችም የተዋቀረ ነው። በየምዕራፎቹም ውስጥ የተለያዩ የጥናቱን ክፍሎች አካቷል። በምዕራፍ አንድ ውስጥ መግቢያ፣የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ መጠነ-ርዕይ፣የጥናቱ ዘዴ፣ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሀሳቦቻቸውን ያካትታል። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የተዛማጅ ጥናታዊ ፁህፎች ቅኝት፣ንድፈ ሀሳባዊቅኝት፤የስነ-ፅሁፍ ምንነት፣የልብ-ወለድ ምንነት፣የልብ-ወለድ አላባዊያን፣ታሪክ፣ትልም፣ ገፀ-ባህሪያት ግጭት፣ጭብጥ እና አንንፃርን አካቶ የያዘ ነው።

በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የ"ተልሚድ"ረጅም ልብ-ወለድ ጭምቅ ታሪክ፣የ"ተልሚድ" ልብ-ወለድን ከልብ-ወለድ አላባዊያን አንፃር ትንተና የያዘ ሲሆን፤ በምዕራፍ አራት ውስጥ ማጠቃለያ፣ የመፍትሄ ሀሳብ፣ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው እና ዋቢ መፅሀፍትን ያካትታል።

### 1.5. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር ዘዴ የሚከተል ነው። ስለገላጭ የምርምር ዘዴ አለም እሸቱ "መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ" በሚለው መፅሀፉ እንዲህ አስፍሮታል።

"ገላጭ ምርምር " ገለፃን፣ትንታኔን እና  አተረጓጎምን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ እያወዳደረ እና እያነጻጸረ ይመለከታል። ገላጭ የምርምር ዘዴ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች የሚያሰባስብ ሲሆን፣ ትኩረቱ ግን የአንዱን ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ ባህሪ መግለፅ ወይም ማሳወቅ ይሆናል።(1994፣148)

ገላጭ የምርምር ዘዴ ጥልቅና ምክንያታዊ የሆኑ ጥናቶችን ለመስራት የሚያስችል የምርምር ዘዴ ነው። አጥኝዋም ይህን የምርምር ዘዴ የመረጠችበት ምክንያት ጥናቱን በጥልቀትና በስፋት ለመመርመር እንዲሁም ለመተንተን ገላጭ የምርምርን ዘዴ ወሳኝ ሆኖ ስላገኘችው ነው። አጥኝዋ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመከተል " ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድን ከልብ-ወለድ አላባዊያን አንፃር ትተነትናለች።

### 1.5.1.የጥናቱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ

አጥኝዋ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የመረጠችውና ወሳኝ ሆኖ ያገኘችው የመረጃ መተንተኛ ዘዴ  መዛግብት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴን ነው። ይሄን የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የመረጠችበት ምክንያት  ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚሰራው እና መረጃ የሚሰበስበው በፅሁፍ ተፅፈው ለሕትመት የበቁም  መፅሀፍትን በመመልከት ነው። ከምልከታ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ውስጥ መዛግብት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ስለ ዶክመንቶች ሰነዶች እና የተለያዩ በፅሁፍ የሚገኙ መረጃዎችን የሚያካትት ነው። አጥኝዋም በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የሚገኙ ፅሁፎችን በመቃኘት ፣የ"ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ በተደጋጋሚ እና በጥልቀት በማንበብ ስለልብ-ወለዱ አላባዊያን ትኩረት አድርገው ለህትመት የበቁ መፅሀፍትን በማንበብ " ተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድን ከልብ-ወለድ አላባዊያን አንፃር ትንተና ትሰጣለች። ያለው እንዳወቀ " የምርምር መሠረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ መዛግብት የመረጃ መሰባሰቢያ ዘዴ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> *መዛግብት ተመራማሪው ሰላለፈም ይሁን ወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። መዛግብት በፅሁፍ መልክ ከየቤተ-መፅሀፍት ፣ቤተ-መዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎችና እንደሁኔታውም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው። በአይነታቸው የህዝብ የሆኑ ወይም ያልሆኑ ፣የግል ጉዳዮችን የያዙ ፣የታተሙ ወይም ያልታተሙ*

*እንዲሁም ታሪካዊ ወይም ወቅታዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ደብዳቤዎች የንግግር ረቂቆች ፣ የግለሰብ የለትተለት ማስታዎሻዎች ቃለ-ጉባኤዎች ፣አዋጆች፣ደንቦች፣ጋዜጦች፣መፅሀፍቶች፣የፍርድቤት ውሳኔዎች እና ሌሎችም በተለያዩ ምክንያቶች በፅሁፍ መልክ ተዘጋጅተው የሚገኙ ሁሉ በመዛግብት መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ስር ይካተታሉ ። (2009፣191)*

### 1.5.1.1. የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በመዛግብት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የተገኘውን መረጃ በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን የመረጠችበት ምክንያት ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከቁጥር ይልቅ በቃላት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ስለሚተነትን ነው። ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴም ከቁጥር ውጭ የሆኑ ጥናታዊ ፅሁፎችን በቃላት መረጃ የሚተነትኑባቸውን ጥናታዊ ፅሁፎችን ለመስራት ምቹ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ስለሆነ አጥኝዋ የዚህን ጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ ለመተንተን ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ወሳኝ ሆኖ አግኝታዋለች። አጥኝዋም ካሉት የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ለጥናቱ የሚቀርበውን ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ በመጠቀም "ተልሚድ " ረጅም ልብ-ወለድን ከልብ-ወለድ አላባዊያን አንፃር ትተነትናለች። ስለ ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ያለው እንዳወቀ "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር" በተሰኘው መፅሀፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

*አይነታዊ መረጃዎች በመልካቸው አብዛኛውን ጊዜ ከቁጥር ይልቅ በቃላት የሚሰበሰቡ ናቸው። በአንትሮፖሎጅ፣በታሪክ፣በፖለቲካ ሳይንስና በተለያዩ ማህበራዊ ሳይንሶች ተዘውትረው በተመራማሪዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው። በአንድ ውስን ቦታ ስለተከሰተ ችግር ወይም ስለሚከናወን ሂደት ጠንካራ፣ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ ይሰጣሉ። ከሁነቶች መከሰት ጀምሮ እስከሚቀጥለው ሂደት በቅደም ተከተል ለማብራራት እና የትኛው ሁኔታ ምን ውጤት እንዳመጣ በግልፅ ለማሳየት አይነታዊ መረጃዎች ጠቃሚ ናቸው።(2009፣410)*

## 1.6. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- ስነ-ፅሁፍ ምንድን ነው?
- ልብ-ወለድ ምንድን ነው?

- ረጅም ልብ-ወለድ ምንድን ነው?
- የልብ- ወለድ አላባዊያን አይነቶች እነማን ናቸው?
- የልብ-ወለድ አላባዊያን በልብ-ወለድ ውስጥ እንዴት ይገለፃሉ?

### 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በምትሰራበት ወቅት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መፅሀፍቶችን አለማግኘትና ከጥናታዊ ፅሁፉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ያለማግኘት ችግር አጋጥሟት የነበር ሲሆን እንደመፍትሄ ከሌሎች ከፍተኛ የመንግስት የትምህርት ተቋማት አፈላልጋ በማግኘትና መፅሀፍቶንም በመዋስ ለችግሯ መፍትሄ አበጅታለች።

# መዕራፍ ሁለት

## 2.1. የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፎች ቅኝት

አጥኝዋ ከዚህ ጥናታዊ ጹሁፍ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸዉን ጥናታዊ ጹሁፎች ለማግኘት ባደረገቺዉ ጥረት ማግኘት የቻለችው ሁለት ጥናታዊ ጽሁፍ ብቻ ነው።በ 2010 ኣ.ም በ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል በሰላማዊት ወርቁ “ባችለር ኦፍ አርትስ” ድግሪ ማሟያ “ተፈጥሮኣዊነት በ ትኩሳት ለብ -ወለድ አስረጅነት”በሚል የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው።ጥናአታዊ ጽሁፉ በ አራት ምእራፎች የተዋቀረ ሲሆን በ ምእራፍ አንድ መግቢያ የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ ኣላማ፣የጥናቱ ጠቀሚታ ፣የጥናቱ መጠን-ርእፍ፣ የጥናቱ የመርጃ ማሰባስቢያ ዘዴዎች፣ጥናቱ የሚያነሰችው ጥያቄዎች ፣በ ጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ፡ በ ምእራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፍ ቅኝት፣ንድፍ ሃሳባዊ ቅኝት፣የ ልብ-ወለድ ኣልባዊያን ፣ የልብ ወለድ ኣፃፃፍ ስልቶች የያዘ ነው። በምእራፍ ሶስት የደራስያን እና ጋዜጠኛ ሰብሃት ለኣብ ገበረ-እግዚያብሄር አጭር የ ሂይዎት ታሪክ ፣ የ ትኩሳት ልብ-ወለድ ጭምቅ ታሪክ፣የ ትኩሳት ልብ-ወለድ ከ ልብ-ወልድ ኣላባዊያን አንጻር ፣ የ ትኩሳት ልብ-ወለድ ከተፈጥሮኣዊንት ኣጻጻፍ ስልት አንጻር፡በ ምእራፍ አራት ማጠቃለያ፣ጥቅሶች በ መገኛ ቋንቋቸው፣ዋቢ መጸሀፍትን ያካተተ ሲሆን የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ እና የ ሰላማዊት ወርቁ ጥናታዊ ጽሁፍ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር የ ሁለቱም ጥናትታዊ ጽሁፍ መግቢያ ስለ ልብ -ወለድ ምንነት ይተነትናሉ ፣በ መእራፍ ሁለት የሚያነሱዋቸው ሃሳቦች ስለ ልብ ወለድ ኣላባዊያን ይተነተናል፣ ሁለቱም ጥናታዊ ጽሁፎች በ አራት ምእራፎችህ የተዋቀሩ ናቸው።ሁለቱም ጥናታዊ ጽሁፎች ከረጅም ልብ -ወልድ ላይ ተኩረታቸውን አድርገው የሚሰሩ ናቸው።ስለ ልብ ወለድ ኣላባዊያን ምንነት የሚያንሱት እና የሚተነትኑት ንድፍ ሃሳብ ከ አንድ አይነት የመርጃ ምንጭ ሰለተጠቀሙ የሚቀራርቡ እና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።የሁለቱ ጥናታዊ ጽሁፎች ልዩነት ደግሞ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ”ተልሚድ”ረጅም ልብ-ወለድን ከ ልብ- ወልድ ኣላባዊያን አንጻር ሲተነትን የ ሰላማዊት ወርቁ ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ “ትኩሳት” ረጅም ልብ-ወልድ ከጠፈትሮኣዊንት የ ልብ-ወልድ ኣጻጻፍ ስልት አንጻር ይተነትናል።

ሁለተኛው ጥናታዊ ጽሁፍ በ አክሱም ዩኒቨርሲቲ በ 2009 ኣም በደርብው ቢሻው ለ ባችለር ኦፍ አርትስ የመጀምሪ ዲግሪ ማሙያነት የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ <<ተልሚድ >>ረጅም ልብ-ወልድ ከ ልብ ወለድ ዘዴዎች ትንተና ነው። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በ አራት ምእራፎች የተዋቀረ ሲሆን በምእራፍ አንድ መግቢያ የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ ኣላማ፣የጥናቱ ጠቀሚታ ፣የጥናቱ መጠን-ርእፍ፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የ መፍትሂ ሃሳቦች፡ በ ምእራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፍ ቅኝት።ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ፣የ ልብ-

ወልድ ምንነትና የ ልብ-ወለድ ዘዴዎች ምንነትን የያዝ ሲሆን በምእራፍ ሶስት የ መረጃ ትንተና ፣ ት<<ተልሚድ >>ረጂም ልብ-ወልድ ጭምቅ ታሪክ እና የ ልብ -ወልድ ዘዴዎች አጠቃቀም በ <<ተልሚድ>>ረጂም ልብ -ወለድ ያጠቃልላል ።በምእራፍ አራት ማጠቃለያ እና አስተያየት፣ዋቢ መጽሃፍትን አካቶ የያዝ ጥናትዊ ጽሁፍ ነው።ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በ አጥኝዋ ጥናታው ጽሁፍ ጋር የ ሚመሳሰላችው ነገር ሁለቱም ጥናታዊ ጽሁፎች በ <<ተልሚድ >>ረጂም ልብ-ወልድ ላይ ትኩረታችውን አድርገው የተሰሩ በ መሆናችው በ ምእራፍ አንድ እና ሁለት የተካተቱ ሃሳቦች ስለ ስነ -ጽሁፍ ፣ስለ ልብ-ወልድ ምንነት፣ስለ ልብ-ወልድ አላባዊያን የሚተነትኑዋችው ሃሳቦች አንድ አይነት የ መርጃ ምንጮችን ስለተጠቀሙ ተመሳሳይነት አላችው።ሁለቱን ጥናታዊ ጽሁፎች የሚያለያያችው ነገሮች ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ<<ተልሚድ >>ረጂም ልብ- ወልድ ከ ልብ -ወለድ አላባዊያን አንጻር መተንተን ሲሆን የ ደርበው ቢሻው ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ <<ተልሚድ>>ረጅም ልብ-ወለድ ከ ልብ-ወልድ ዘዴዎች አንጻር ይተነትናል። እነዚህም የ ልብ-ወለድ ዘዴዎች ገለጻ፣ምልልስ፣ምልሰትና ንግር ናችው። የ አጥኝዋ ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ ስለ ልብ-ወለድ አላባዊያን ስለ ታሪክ፣ትልም፣ገጸ-ባህሪያት፣ግጭት፣መቼት፣ጭብጥ እና አንጻር ይተነትናል።

## 2.2.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.2.1. የ ስነ ጽሁፍ ምንነት

ስነ ጹሁፍ የ ሰው ልጅ የ እለት ተልት ኑሮ ፣በ አለም ላይ ያለውን ክስተት ሁሉ አንጸባርቆ የ ሚያቀርብ ሲሆን ከ እውነታው አለም በመነሳት ደርሲው የራሱን የፈጥራ ታሪክ ጨምሮበት ለ አንባቢያን የሚያቀርብበት የ ጥበብ ሰራ ነው። በርሃኑ ማቲዎስ <<fundamentals of literature >>በተሰኘው መጽሃፍ ስነ ጽሁፍን እንደሚከተለው አስፈሮታል።

> *ሊትሬቸር <<ሊትራ>>ከ ሚለው የ ላቲን ቃል የተገኘ ሲሆንይህ ማለት የ አልፋ ቤት ፊደሎች ማለት ነው።የ አለፋ ቤት ፊደላት በ አንድ ቋንቋ መጻፍ የ ሚለውን ያምለክታል ይህ ማለት ሊትሬቸር የ ሚለው ቃል የተገኘው መጽሃፍ ከሚልው አንድምታ እንደሆን ያመልክታል ። በ ሌላ መልኩ የ ቃሉ መነሻ መጻሃፍ ከሚለው ድሪጊት ጋር የ ጠበቀ ቁርኝት እንዳለው ይገልጻል።(2009,16)*

ይህ ሃሳብ አንድሚያመልከተው ስነ ጽሁፍ ከሚለው ድርጊት ጋር ቀትተኛ የ ሆነ ግንኙነት ያለው የጥበብ ዘርፍ ነው።ስነ -ጽሁፍ በ አለፋ ቤት ፊደሎች ገብታ ላይ ያሉት ፊደላት ስብስብ ነው ሲባል ምጽሃፍ ከሚለው ድርጊት ጋር ግንኙነት መጽሃፍ ለሚለው ተግባር የምንጽፍበት ቋንቋ ፊደላት ማለፈልጉ ነው ። ዘሪሁን አስፋው <<የ ስነ -ጽሁፍ መሰርታዊያን >>በተሰኘው መጽሃፍ ስነ-ጽሁፍን እንደሚከተልው

አሰፍሮታል። "ስነ -ጽሁፍ በተለያዩ ቅርሶች በቋንቋ አማካኝነት የሚክሰት ስለ ሰዎች፣በሰዎች የሚዘጋጅ የገጠመኝ ማንጸባረቂያና ህይዎትን እውነተን ባንዱ አጣምሮ የሚይዝ ህልወናው በ ቃለም በ ጽሁፍም የሆነ ፈጠራ ሰራ ነው ማለት እንችላለን።"(2005,3)

ስነ-ጽሁፍ የሰው ልጆችን የ እለት ተእለት ሂይዎት በ መቅዳት እና ስነ-ጽሁፋዊ ቅርጽ በማሰያዝ በቋንቋ እና በ ጽሁፍ የ ሚያቀረብ ዘርፍ ነው ። ስነ -ጽሁፍ ውበት ባለው ቋንቋ በቃለም ሆነ በጽሁፍ የሚቀርብ ዘርፍ ነው ።በቃል የሚተላልፉ የ ስነ-ጽሁፍ ዘርፎች ቃላዊ ስነ-ጽሁፍ በመባል ይትወቃሉ ።በመሆኑም ስነ-ጽሁፍ በዉስጡ የተለያዩ ዘርፎች ያሉት ሲሆን እዚህም ልብ-ወለድ ፣ረጅም እና አጭር ልብ-ወለድ ተውኔቶች ፣ግጥም ለጽሁፋዊ ስነ -ጽሁፍ በምሳሌነት ይተቀሳሉ።ቃላዊ ለሆኑ ስነ-ጽሁፎች ደግሞ አፈ -ታሪክ፣ምሳሊያዊ አነጋገር፣ተርት፣እንቆቅልሽ ተጥቃሽ ምሳሊዎች ናችው ።ዘሪሁን አስፋው <<የ ስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን >>በተሰኘው መጽሃፍ ስለ ስነ-ጽሁፍ አንደሚከትለው አስፈሮታል። ሰነ-ጽሁፍ በሰው ልጆች ታሪክ ረጅም ዘመናት የቆየ የ ኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው ።ሰለመንነቱ ስለ አፈጣጠር ሚስጥሩ ስለሚያካትታቸው ነገሮች በሰዎች ዘንድ ስለ ሚያሳደርው ተጽእኖ ስለ ሚሰጥው አገልግሎት ያልተባለ ነገር የለም ። (2005,1)

ከዚህ ሃሳብ የ ምንረዳው ስነ-ጽሁፍ ረጂም ዘመናትን ያስቆተረ መሆኑን ነው ። ስነ -ጽሁፍ ማህበራዊ ነው።ይህ ማለት ከማህበረሰቡ የ ወጣ ሃሳብ በሰው ተዘጋጅቶ ለ ሰው የሚቀርብ ጥበብ ነው ።ስነ - ጽሁፍ የ ሰው ሃዘን እና ደስታ ፣ጥላቻ እና ፍቅር፣ድል እና ሽንፈት ፣ርሃብ እና ጥጋብ፣ምኞትና ጉስቁልና፣ሂይዎት እና ሞት እንዲሁም ሰናይ እና እኩይ ባህሪያቱን ሌሎችንም የ ሂይዎት ገጽታዎች የማሳየት አቅም አለው ።የ ሰው ልጅ በ ማህበርሰቡ ዘንድ በሚኖርበት ወቅት የሚያጋትሙትን ችግሮችም ሆነ ሌሎች የሚተገብሩዋቸው ነገሮች በ ስነ - ጽሁፍ አማካኝነት ይገልጸዋል።

### 2.3. የ ልብ-ወለድ ምንነት

ልብ-ወለድ በእውኑ አለም የሚንቀሳቀሱትን የ ግለሰብን ሂይዎት እና በደራሲው ምናብ የሚፈጠሩ የፈጠራ ታሪኮችን በ ቃላት አማካኝነት የሚያንጸባርቅ እና ምናባዊ ስእል ሆኖ የሚታይ የ ኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነው። ልብ-ወለድ በማህበራዊ ሂይዎት ውጣውረድ ወስጥ የሚያጋጥሙትን ውስብስብ ጉዳዮችን እና ክንውኖችን በ ገጸ-ባህሪያት አማካኝነት አስመሰሎ ማቅረብን የሚያጠቃልል ነው። ይህን አስምልከቶ ዘሪሁን አስፋው <<የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን>> በ ሚለው መጽሃፉ እንደሚከትለው እሰፍሮታል።

*ልብ-ወለድ ከደራሲው መናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የ ሰው ሂይዎት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳሰሎ ለመቅርጽ የሚያስችል ብቁሙ እውነት ያልሆነ የ ኪነ- ጥበብ ዘርፍ መሆኑን እንገነዘባለን ።ልብ ወለድ በቁሙ እውነት አደልም ሲባል የተተረከው ገጸ-ባህሪ ሂይዎት በ እውኑ አለም በ እርግጥ የ ተፈጸመው ወይም ታሪኩ የሚያልቀው ዘመን እና ቦታ እንዳለ እየታየ አደለም ለማለት ነው። (2005,153)*

ልብ-ወለድ በዉስጡ የ ሚይዘው በ ልብ-ወለድ ታሪክ ወስጥ ደርጊቱ የተፈጸመው ወይም የተፈጸመበት ሰው በ እውነቱ አለም የ ሌለ በገጽ-ባህሪያት የሰውን ባህሪ ለብሰው እና ምስለው የሚሳሉት የደራሲው ምናባዊ ፈጥራ ሆነው ነው ።ልብ-ወለድ ደራሲው ከእውንተኛው አለም ነጻብራቅ በመነሳት በራሱ ችሎታ እና አቅም የመረጠውን ታሪክ ሂደት ነው ።ልብ-ወለድ ህይዎትን በተለይ ደግሞ የ ሰው ልጆችን ማህበራዊ ህይዎት በ ውብ ቋንቋ የሚያቀረብ አንዱ የስነ-ጹሁፍ ዘርፍ ነው።

ብርሃኑ ገብረ-ጻዲቅ <<አጠቃላይ ያማረኛ ቋንቋ >>በተሰኘው መጽሃፍ ልብ-ወለድን አጭር እና ረጅም ልብ-ወለድ በማለት ይከፍላቸዋል ።

### 2.3.2. ረጅም ልብ-ወለድ

ብርሃኑ ገብረ-ጻዲቅ <<አጠቃላይ ያማረኛ ቋንቋ >>በተሰኘው መጽሃፍ ረጅም ልብ-ወለድን እንደሚከተልው አሰፍሮታል፣ረጅም ልብ-ወለድ ብዙ ገጽ-ባህሪያትን የሚያሳትፍ ታሪኩ በተለያየ ቦታዎች እና በተለያየ ጊዚያት የሚፈጽም ፣ሰፊ እና ውስብስብ ግጭቶችን የሚይዝ ፣ብዙ ቅርንጫፍ ጭብቶችን የሚይዝ ፣ብሃት ባላቸው ገጾች እና ከ ሰማኒያ ሺ ገጾች (80,000) ባላነሱ ቃላት የሚጻፍ የ ልብ-ወለድ አይነት ነው ።(2008,109) ረጅም ልብ-ወለድ ሰፊ የሆነ ታሪክ ከ መጀመሪያው እስከ መጨረሻ የሚተርክ እና በዙ እና የተለያዩ አብይ እና ንኡስ ጭብቶች ያሉት ፣ታሪኩን የሚያስቀጥሉልን ገጸ-ባህሪያትም እንደ ታሪኩ ስፋት መጠን የ ብዙ እና የተለያዩ ባህሪያትን የተላበሱ ናቸው፣ረጅም ልብ-ወለድ ሰፊ መቸት የሚጠቀም ግጭቶችም የተወሳሰቡ ናቸው ።ዘሪሁን አሰፋውም <<የ ስነ-ጽሁፍ መሰርታዊያን >>በሚለው መጻፍ ረጅም ልብ-ወለድን እንድ ሚከተለው አሰፍሮታል ። ረጅም ልብ-ወልድ እርስ በራሱ የሚደጋገፍ ከ አንድ በላይ ታሪኮችን የሚይዝ ፣በርካታ ገጽ-ባህሪያትን የሚያሳትፍ ፣መቼቱ እጅግ ሰፊ እና ታሪኩ እያዘገመ የሚሄድ የ ልብ-ወለድ አይነት ነው ።(2005,152)

ረጅም ልብ-ወለድ ሰፋ ያለ ታሪክ ያለው ብዙ ገጽ-ባህሪያት ያሉት አንድን ታሪክ ከ ልደት እስከ ሞት ሙሉ ታሪኩን የሚተርክ የ ልብ-ወለድ አይነት ነው ።

### 2.3.1. አጭር ልብ-ወለድ

ዘሪሁን አስፋው <<የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን >>በተሰኘው መጽሃፍ አጭር ልብ-ወለድን እንደሚከተለው አስፍሮታል። አጭር ልብ-ወለድ ማለት ስብስብ ያለ ወይም የታውቀ ጥብቅ ትስስር ያለው ፣ፍጥነት ጎልቶ የሚታይበት፣አንድ ብቻ የትኩረት ነጥብ ያለው ፣በ አጭር ታሪክ የተዋቀረ እንዲሁም ሶስቱንም የ አጭር ልብ- ወለድ ባህሪያትን ቁጥብነትን ፣ጥድፊያ፣እና ነጠላ ውጤትን ያሟላ ነው ።(2005,228)

አጭር ልብ-ወለድ ከ አሰር ሺ (10,000) ቃላት የማይበልጡ ታሪኮችን የያዙ አንድ ዋነኛ ግብ ለማምጣጥ የተዋቀረ እና ፍጥነት የሚታይበት አጭር ታሪክ ያለው እና ያልተወሳሰበ በፍጥነት ተጅምሮ በፍጥነት የሚያልቅ ታሪክ ያለው ፣መቼቱ የተወሰነ ፣ትንሽ ገጽ-ባህሪያትን የሚያሳትፍ የ ልብ-ወለድ አይነት ነው።

### 2.4. የልብ-ወለድ አላባዊያን

ዘሪሁን አስፋው <<የ ስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን>>ከተሰኘው መጽሃፍ የ ልብ-ወለድ አላባዊያን እንደሚከተለው አስፍሯቸዋል ።

> *የልብ-ወለድ አላባዊያን ወይም ፍሬ ነገሮች የሚታወቁት ታሪክ ፣ትልም ፣ገጸ-ባህሪያት ፣ግጭት፣መቼት፣ ጭብጥ እና አንጻር ናቸው ። አንድ ልብ-ወለድ ልብ-ወለድ መሆን ሚችለው እነዚህን የ ልብ-ወለድ አላባዊያን ወይም ፍሬ ነገሮች አወቃቀር እና ህልውና ፣አንድነት እና ግጥምጥምነት የኖረ እንደሆነ ነው ።ይህ አንደነት እና ግጥምጥምነት ሊገኝ የሚችለው ከያኒው ከሚመርጣቸው ጥበባዊ ዘዴዎች አማካኝነት ፍሬ ነገሮች ተቀነባብረው ሲቀርቡ ነው።(2005,154)*

የ ልብ-ወለድ ፍሬ ነገሮች ወይም አላባዊያን ተብለው የሚታወቁት ታሪክ ፣ትልም፣ሴራ፣ገፀ-ባህርያት ፣ ግጭት ፣መቼት ፣አንጻር ሲሆኑ እንዚህ ለ አጠናን እንዲመቹ ተለይተው ተጠሩ እንጂ በልብ-ወለድ ውስጥ በተናጥል ታይተው ለእየብቻቸው የሚገኙ አደሉም ።አንዱ የ ልብ-ወለድ አላባያ ያለ አንዱ ፍቺ የማይሰጡ እና ብቻቸውን የማይቆሙ ኣርስ በራሳችው ተደጋግፈው ትርጉም የሚሰጡ ናቸው ።ሰለ ታሪክ ሲወሳ የ ታሪኩ ባለቤት የ ሆኑት ገጽ-ባህሪያት አብረው ይነሳሉ።የገጽ-ባህሪያቱ ታሪክ ስንመለከት ታሪኩ የሚፈጸምበት ጊዜ እና ቦታ ወይንም መቼቱን አብረን እናነሳለን ።የገጽ-ባህሪያቱን ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜ እና ቦታ የምንተርክበት ዘዴ ወይንም አነጻር እናነሳለን ።አንዱ ያለ አንዱ መቆም ስለማይችሉ በዚህ መንገድ ሌሎችም የልብ-ወለድ አላባዊያን ቁርኝታቸው የጠበቀ ነው ።

### 2.4.1. ታሪክ

ታሪክን ዘሪሁን አሰፋው <<የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን>>በተሰኘው መጽሃፍ እንደሚከተለው አሰፍሮታል ።

> *ታሪክ ለ ልብ-ወለዱ ቀዳማዊ ነገር ነው ።የልብ-ወለዱ መሰረታዊ ገጽታ አንድ ኣይነት ታሪክ መተረኩ ነው ።ታሪክ በሰው ልጅ ገጠመኝ ሊከሰት የሚችል ወይም የ ሰው ልጅ በ ምናቡ ሊያስበው እና ሊፈጥረው የሚችል ሲሆን የአንባቢ አእምሮ ፈቅዶ ይቀበለዋል ።በእውኑ አለም ሰዎች ዘንድ ሊያጋጥም የሚችልን ድርጊት ወይም የሂይዎት አቅጣጫ ወይም የኑሮ መስክ ተኣማኒ ይሆናል ። ታሪክ ደራሲው በመረጠው የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተቀናጅተው የሚቀርቡትን እና በገጽ-ባህሪያቱን የሚፈጸሙትን ድርጊቶች አነሳስ ፣አፈጻጸም እና የመጨረሻ ውጤት ይይዛል ። (2005,154)*

ታሪክ ማለት ልብ -ወለድ ለመጻፍ ምክንያት የሚሆነን ዋና ሃሳብ እና የልብ-ወልዱ የ ህልውናው መሰረት ነው ። ታሪክ የነግሮች ክስተት ሲሆን ፣በልብ-ወለዱ  ውስጥ ደግሞ የድርጊቶችን ሂደት ቅደም ተከትል ማን ምን አደረግ እያለ የሚተርክ የ ልብ-ወልዱ መሰርት ነው ።ታሪክ የድርጊቶች ቅደም ተከተል ነው ስንል አንድ ታሪክ መጀምሪያ መሃል እና መደምደሚያ አለው ።ታሪኩ ሲጀመር የነበሩ ክስተቶች ምሃል ላይ ሲደርሱ እየተጧጧፈ ኡዲስ ታሪኮችን እየጭመሩ ሲኸዱ በመደምደሚያው ክፍል ደግሞ የመፍትሄ ሃሳቦችን የድርጊቶች ፍጻሜን በተራ ቅደም ተከተል ሰለሚያሳየን ነው ።በልብ-ወለዱ ወስጥ የተለያዩ ስሜቶችን የሚይዝ አሳዝኝ ነው  ፣ያስደስታል ፣አስተማሪ ነው ፣የ ሚያዝናና ነው ብለን የምንገልጸው የልብ-ወልዱ ክፍል ታሪክ ነው ።ከመጀምሪያ እስከ መጨርሻ አዳዲስ ነገሮችን እያመጣ የ ልብ-ወለዱን የድርጊቶች ቅደም ተከተል የሚያስቀጥልልን ታሪክ እንለዋልን ።

### 2.4.2. ትልም

ዘሪሁን አሰፋው ትልምን የስነ -ጽሁፍ መሰረታዊያን ከተሰኘው መጽሃፍ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> *ትልም በ አንድ ልብ-ወለድ ውስጥ ምን ?ለምን? ተደረገ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘወን መልስ የሚያካትት ወይም በጊዜ ቅደም ተከትል የተፈጸሙ ሁነቶችን የተደረጉበትን ምክንያት እና የሚያስከትሉትን ውጤት  ጥብቅ ቁርኝት የያዝ የልብ-ወለድ አካል ነው ።ትልም የሁነቶች ትረካ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱ  ግን በምክንያትና ውጤት ላይ ነው ።ንጉሱ ሞተ ከዚያ በሱ ሀዘን ንግስቲቱ ሞተች ትልም ነው ።በኋለኛውም የጊዜ ቅደም ተከተል እንዳለ ነው ነገር ግን የነገሩ ምክንያታዊንት ነው ጎልቶ የወጣው ፣ወይም በሌላ አገላለጽ ንግስቲቱ ሞተች ሲባል በንጉሱ መሞት አዝና መሆኑ እስከትገለጹበት*

*ጊዜ ድረስ በምን ምክንያት እንደሞተች ማንም አያውቅም።ይህ አንድ ድብቅ ጉዳይ ያዘለና ላቅ ብሎ ሊሰፋፋ የሚችል ቋጠሮ ያለው ትልም ነው ።(2005,157)*

ትልም በምክንያት በውጤት የተመሰረተ አንድ ነገር ለተደረገበት ምክንያት መልስ የሚሰጥ ምን በምን ምክንያት ተደረገ ? ከዚያስ ምን አይነት ለውጥ አመጣ ? የሚለውን ሃሳብ አካቶ የሚይዝ የ ልብ-ወለዱን የ ነገሮች ቅደም ተከተል የምናገኝበት የልብ-ወልድ አላባዊያን ውስጥ አንዱ ነው ።

### 2.4.3. ገጸ-ባህርያት

ስለ ገጽ-ባህሪ ፈንታሁን እንግዳ <<የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ >> በሚለው መጽሃፉ እንዲ አስፍሮታል።

> *ገጸ-ባህሪ የሚለው ቃል በፈጠራ ታሪክ ውስጥ ያሉትን ሰውች ማለትም አበበ፣ከበደ፣ ጅብ፣በግ፣ቀበሮ፣በድርሰቱ ውስጥ የሚቀርጹት ሰማያዊ ወይም ሀተታ ተፈትጥሮኣዊ ፍጥረታትና መናፍስት ከሆነ ሰይጣን፣ ምላእክት፣ሰናይ መናፍስት ፣ተንኮልን፣ደግነትን ፣መልካም ሰራን ፣ቁንጅናን የመሳሰሉትን ይወክላል።ገጸ-ባህሪያት ብርልብ-ወልዱ አለም ሲጋ ለብሰው ፣ባህሪያትን ተጎናጽፈው መጠሪያ ተሰጧቸው፣መኖሪያ፣ ተበጅቶላቸው ፣የሚንቀሳቀሱ፣የሚተነፍሱ ፣የሚናገሩ፣የሚበሉ፣የሚጠጡ፣እንደ እውኑ አለም ሰዎች የሚኖሩ፣የሚሞቱ፣የሚያፈቀሩ ፣የሚርባቸው፣የሚያፈቅሩ፣የሚጣሉ የሚደሰቱ የሚያዝኑ የልብ-ወለድ አለም ሰዎች ናቸው።(2009,25)*

ገጸ-ባህሪያት ማለት የ ገሃዱ አለም ወኪል ሰዎች ሲሆኑ የተጻፈላቸውን ሃሳብ ነፍስ እንዲዘሩበት ህይወት እንዲኖረው አድርገው ተላብሰው ስሜቱን ሀዘኑንም ደስታውንም ሆነው ህይዎታቸው እስኪመስል ደረስ የሰውን ታሪክ ተላብሰው የሚጫወቱልን ፣የ ልብ-ወለዱን ሙሉ ታሪክ ተሸክመው የሚያራምዱ በእውነተኛው አለም ያሉትን ሰዎች ወክለው እና የተለያዩ የሰው ልጅ ባህሪያት እና እና እረቂቅ ሰሜቶች ተላብሰው የሚጫወቱ በደራሲው ምናብ ወስጥ የተሳሉ የ ልብ-ወለድ አለም የደራሲው የ ፈጠራ ሰዎች ናቸው ይህ ሲባል ግን ግጸ-ባህሪያት የ ገሃዱ አለም ሰዎች አምሳሎች ወይም ተወካዮች በመሆናቸው ደራሲው የፈጠረላቸውን አለም አለማቸው በማድረግ የሚንቀሳቀሱ ደራሲው ስለ ህይዎት ያለውን አመለካከት የሚገልጽባቸው ምናባዊ ፍጡራን አንጂ በደርሰቱ ውስጥ በተሰጣቸው ስም ወይም የመኖሪያ አድራሻ ወይም ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታ በገሀዱ አለም ብንፈልጋቸው የምናገኛቸው ሰዎች አደሉም ።

በልብ-ወለድ ታሪክ ውስጥ የሚሳሉ ገጸ-ባህሪያት ህልውና ለታሪኩ አንዳች ፋይዳ ሊኖረው ይገባል ። ለ ልብ-ወለዱ የ ገጸ-ባህሪያት አስፈላጊነት ከግምት ውስት መግባት አለበት ። ብዝተው የ ልብ-ወለዱን መያዣ መጨበጫ እንዳያሳጡት ፣አንሰውም ጎዶሎ እንዳያደርጉት በተገቢው ቁጥር መጠን መቅረብ አለባቸው ።ለ ታሪኩ ፍሰት ምስል እና ማገር ሆነው መዋቅሩን የሚገነቡ ፣ለ ታሪኩ ህያውነትን ዋና የሆኑ ገጸ- ባህሪያት የመኖራቸው ያህል ድርሻቸው አናሳ የሆነ ገጸ-ባህሪያትም አሉ ።

ዘሪሁን አስፋው <<የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን>>በተሰኘው መጽሃፉ ፈርጀ በዙ ገጸ-ባህሪያትን እንደሚከተለው አስፍሮታል ።

ዘሪሁን አስፋዉ<< የስ-ጹሁፍ መሰረታዊያን >> በተሰኘዉ መጸሃፉ ገጸ-ባህሪያትን በልብ ወልድ ዉስጥ ካላቸዉ ሃላፊነት እና የቆይታ ጊዘ አኩዋያ ፈርጀ ብዙ እና ፈርጅ አንድ ብሎ በሁለተ ከፍሏቸዋል።

### 2.4.3.1. ፈርጀብዙ ገጸ-ባህርያት

ፈርጀ በዙ ገጸ-ባህሪያት ቃሉ እንደሚያመለክተው ከ ተለያዩ አቅጣጫዎች የተቀረጹ ፣ውስብስብ ባህሪ ያላቸው ።እንዲ ያሉት የልብ-ወለዱ አለም ሰዎች በተወሳሰብ የኑሮ ውጣ ውረድ የተጠመዱ ፣አላማቸውን ከ ግቡ ለማድረስ ሲዋትኑ ብዙ እንቅፋቶች የሚያጋጥማቸው ሰለ ሰው ልጅ በ አጠቃላይ ሰለ ህይዎቱ ሰለ ተፈጥሮ ሲፈላሰፍ የሚገኙ ከ ህይዎት አያሌ ገጽታዎች ንክኪ ያላቸው በቀላሉ የማይታወቅ ገጽ-ባህሪያት ናቸው ።(2005,171)

ፈርጀ ብዙ ገፀ-ባህርያት በአንድ ድርሰት ውስጥ በብዙ ቦታዎች የሚታዮ፣አብዛኛው ታሪክ የእነሱን የሆነና በብዙ ሁነት ዉስጥ ለረዥም ጊዜ የሚታዮ ገፀባህርያት ፈርጀ ብዙ ገፀባህርየት ይባላሉ።ፈርጀ ብዙ ገፀባህርያት ታሪኩ ተደምሮ እስኪያልቅ የሚቆዩ፣ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተቀረፀ የድርሰቱን ዋና ታሪክ የማይዙ የገፀባህርያት አይነቶች ናቸው።ዘሪሁን አሰፋው "የስነጽሁፍ መሠረታውያን" በተሰኘው መፅሐፍ ስለፈርጀ አንድ ገፀባህርያት እንደ ሚከተለው አስፍሮታል።

### 2.4.3.2. ፈርጀ አንድ ገፀባሕርያት

ፈርጀ አንድ ገፀባሕርያት ብቅ ባሉ ቁጥር ወዲያው ሊለዮ የሚችሉ በቀላሉ የሚታወሱ፣በተደጋጋሚ የሚታይ አንድ የተወሰነ ልማድ ወይም ባህርያላቸው፣የተለያዩ ሁነቶች እና አጋጣሚዎች ውስጥ ቢገቡም የማይለወጡ ገፀባሕርያት ገፀባሕርያት ናቸው። እነዚህ ገፀባሕርያት ከብዙ አቅጣጫዎች ያልተቀረፁ፣

በእውኑ ዓለም በእለት ተለት ህይወት ዘወትር የሚገኙ፣ውስብስብነት የሌላቸውና አብዛኛውን ጊዜ አንድ ወይንም ሁለት የታወቀ ድርጊት የሚገልጽ በአንድ ዓረፍተ ነገር ሊገለፁ የሚችሉ ናቸው።(2005፣172)

ፈርጀ አንድ ገፀባሕርያት  ሁልጊዜ ይዘውት ብቅ የሚሉት ታሪክ በአንድ ነጠላ ጉዳይ ላይ ያተኮረ እና በተደጋጋሚ አንድ መለያ ባህርያትን የሚደጋግም ስለሆነ አንባቢን አያስደንቅም ወይም ተደጋጋሚ በመሆኑ አሰልቺ ይሆናል።ገፀባህሪው ብቅ ባለቁጥርም ኤጭ!እንግዲ ጀመረ ያስብላል እንጂ በጉጉት አሁን ደግሞ ምን ሊያመጣ ይሆን አያሰኝም።ፈርጀ አንድ ገፀባሕርያት በታሪኩ ውስጥ ብዙ ሃላፊነት እና ሚና የላቸውም ።ዘርፈ አንድ ገፀባሕርያት ከሰማቸዉ እንደምንረዳው አንድን ባህሪ ይዘው የሚመጡ በመሆናቸው እና በልብ-ወለድ ታሪክ ላይ ዘላቂነት የሌላቸው ውጠት ገኸት የሚሉ ስለሆኑ በሐልብ-ወለድ ታሪክ ውስጥ የሚሰጣቸው ሚና እና ድርሻ  ትንሽ ነው።

**2.4.4. ግጭት**

ዘሪሁን አሰፋዉ <<የስነ ፅሑፍ መሰረታዊያን በተሰኘዉ መፅሀፉ ግጭትን እንደሚከተለዉ አሳትፎታል

> *ግጭት በልቡወለዱ አለም የሚኖሩ ገፀ ባህሪያት በታሪኩ ዉሰስጥ በተፈጠረላቸዉ እርስበርሳዊ ግንኙነት የተሳ በተለያዩ ምክንያቶችቅራኒወች ወይም አለመግባባቶች ሳቢያ የሚፈጠሩ ፍጨት ወይም ፍልሚያ ነዉ።ግጭት በሁለት ተፃራሪ ሀይላት መካከል በሚደረገዉ ትግል አንዱ ሌላዉን ለማሸነፍ አነዱ ሌላዉን ለመጣል ወይም አንዱ ሌላዉን ፣ሌላዉ ሌላዉን  ለማሸነፍ ላለመዉደቅ ወይም ላለመሸነፍ የሚደረግ ጥረት ነዉ። ግጭት ገፀብህሪያት ከገቡበት የፍልሚያ ማጥ ለመዉጣት ሲጣጣሩ ሌላ ችግር  ሰደነቀርባቸው፣ እንደገና ለማርገብ ሲሞክሩ የማይታይበት የልብ ወለድ አይነተኛ ፍሬ ነገረ ነው።ግጭት መዋቅሩ የሚገነባበት ጥሬ ነገርም ነው ይባላል።በታሪኩ መዋቅር በሂደት የሚከናወኑት ድርጊቶች መነሻቸው ግጭት በመሆኑ ነው እንዲ የተባለው። (2005፣172)*

ግጭት ሁለት ወይም ከዚያን በላይ በሆኑ ሰዎች፤ወይም ቡድኖች፣ግለሰቦች መካከል አንዳንድ ጊዜም ውስጣዊ ከሆኑ ስሜቶች ጋርየሚፈጠረው አለመስማማት ወይንም ፀብ ወይም የሰላም መደፍረስ ነው። ግጭት አንድ ገፀባህርይ የራሱን አላማ እና በፍላጎት ለማሟለት ሲል ከተለያዩ ነገሮች ጋር የሚፈጥረው አለመግባባት ሌላውም የራሱ የሆነ ነገር ላለመስጠት ሌላው ደግሞ ለመውሰድ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ግጭት ይባላል።እነዚህ ትግሎች እና ውጣ ውረዶች በህይወት ለመኖር  ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ፣የተሻለውን ለመያዝ፣የተመኙትን  ለማሳካት በአጠቃላይ ፍላጎትን ለሟሟላት ወይም የልብን ለማድረስ አንዱ ሌላው ጋር የሚፈጥረው ግብግብ ግጭት ይባላል።

ዘሪሁንአስፋው"የስነፅሁፍመሠረታዊያን"በተሰኘው መፅሐፍ የግጭት አይነቶችን እንደሚከተለው አስፍሮታል።

### 1.4.4.1. የግጭት አይናቶች

በልብወለድ ዉስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች የተለያዩ ናቸዉ።ባህሪያቱእንተሳሉበት ሁኔታ፣እርስበርስ እንዳላቸዉ

ግንኙነት እንደእምነታቸዉና እንደፋላጎታቸዉ ከሁሉምበላይ ደግሞ

እንደታሪኩ አይነትና ሊቀርሱ እደተፈለገዉ ጉዳይ ወይም

የማህበረሰብ ገጽታ ይለያያለ።ሰዉከሰው ጋር የሚያደርገው

ግጭት፣ሰዉከራሱጋር የሚያደርገዉ ግጭት፣ሰዉ ከተፈጥሮ

ከስተቶች ጋር የሚያደርገዉ ግጭትእና ሰዉ ከማህበረሰቡ ጋር

የሚያደረገው ግጭት ናቸው።(2005፣175)

ግጭት እንደ የሰው የውስጥ ስሜት እና ፍሐላጎት የሚፈጠረው ቅራኔ በተለያዩ ቁጥር የሚፈጠሩ የግጭት አይነቶችም ይለያያሊ።የሰው ልጅ ሞኖች እና ፍላጎቱን ለማሟላት ሲል ከተለያዩ አካላት ጋር የተለያዩ ግጭየቶችን ይፈጥራል።የሚፈጠሩት ግጭቶየችም እንደመሰላል ሁነው ታሪኩን ከአንድ ጥግ ወደ ሌላኛው ጥግ የሚያሳድጉ ናቸው።

### 2.4.4.2. ሰው ከሰው ጋር ያለው ግጭት

ዘሪሁኑ አስፋው"የስነፅሁፍ መሠረታዊያን"ከተሰኘው መፅሐፍ ሰው ከሰው ጋር ያለውን ግጭት አንደኛው የግጭት አይነት በሰውና በሰው መካከል የሚፈጠረውና ሰው ከሰው የሚባል ነው።ይህ ሁለት ሰዎች ባላቸው የእምነት፣የፍላጎት፣የአለማ ወይም የአቋም እንዲሁም የአስተሳሰብ እና የስብእና ልዮነት ምክንያት የሚፈጥር ነው።(2005፣175)ሰው ከሰው ጋር የሚያደርገው ግጭት አንድ ሰው የራሱን አላማ እና ፍላጎት ለሚሚላት ወይም የራሱን የሆነ ነገር ላለማስነካት ከልላ ሰው ጋር የሚደርገው ግብግብ ወይም

አለመለማመጥ ነው።ሰው ከራሱ ጋር ያለው ግጭት አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ባለው የሀሳብና የአስተሳሰብ ልነዩነት ነገሮችን የማድረግ ፍላጎት እና ያለማድረግ ፍላጎት የሚፈጥሩት የሀሳቡ ግጭት ነው።

### 2.4.4.3. ሰው ከራሲጋር የሚያደርገው ግጭት

ዘሪሀን አሰፋው"የስነፅሑፍ መሠረታዊያን"በተሰኘ መፅሐፍ ሰው ከራሱ ጋር ያለውን ግጭት እንደሚከተለው አስፍሮታል።

ሰው ከራሱ ጋር የሚየደርገው ግጭት ህሊናዊ ወይም ስነልቦና የሚባለው ግጭት ነው ።ይህ አይነት ግጭት በአንድ ሰው ዉስጥ በሚኖሮ ፍላጎቶች መካከል የሚፈጠር ቅራኔ ነው። በእውኑ የሚከናወነዉ ተግባርና በፋላጎት መካከል አለመጣጣም ሲኖር በገፀባህሪው ውስጥ የስብእና ችግር ይከሰታል።ገፀባህርው በውስጡ ያለው የራስ ግምት በመሆንና በመምሰል መካከል ተወጥሮ ትግል ውስጥ እንዲገባና እንዲጨነቅ፣አንደኛውን የበላይ ለማድረግ እንዲፋጨረጨር ያደርገዋል።ገፀባህሪው ስለ እራሱ ስብእናና ማንነት ያለው ግምትና ሌሎች ገፀባህርያት ስለ እሱ ያላቸው ግምት ህሊናዊ ግጭቱን ይፈጥራሉ።

(2005፣175)

ሰው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ግጭት በአንድ ሰው ውስጣዊ ሀሳብ ላይ የሚኖሩ ፍላጎቶች መካከል የሚፈጠር ቅራኔ ነው።አንድ ሰዉ ከራሱ ጋር ላድርግ አላድርግ፣ልሁን አልሁን፣ልናገር አልናገር በሚሉ ሀሳቦች ከራሱ ጋር የሚያደርገው የሀሳብ ሙግት ነው ።አንድ ገፀባህርይ በሁለት አማራጮች ተወጥሮ አንደኛውን ትቶ በሌላኛው ለመገጋዝ ወይም ለመወሰን ረቂቅ ከሆኑ ስሜቶች ጋር ከመጥላት፣ከመውደድ ፣ ከመደሰት፣ከማዘን ስሜቶች ጋር ውስጡ በተፈጠሩት ታሪኮች ለመተው እና ላለመተው ከራሱ ጋር የሚያደርገው ግጭት ከምኞ እና ፍላጎት ጋር የሚገናኝ ህሊናዊ ወይንም ውስጣዊ ግጭት ነው።

### 2.4.4.4. ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የሚያደርገው ግጭት

ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የሚያደረገው ግጭት የአንድን ማህበረሰብ መለያ የሆኑ ታሪክ፣ባህል፣ወግ የአለባበስ ስነስርዓት፣ የአመጋገብ ስነስርዓት ፣የሰርግ እና የለቅሶ ስነስርዓት ከሌላ ባእድ ከሆነ ባህል ጋር ማወራረስ ወይም መተካት ከማህበረሰቡ ባህል ውጪ የሆኑ ነገሮችን እንዲቀበሉ ማድረግ የሚፈጥረው ቅራኔ ወይም አለመግባባት ነው።ሰው ከማህበረሰቡ ጋር  የሚያደርገው ግጭት አንድ ሰውወም ቡድን የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ወይም ባህል በራሱ እምነት  እና ፍላጎት ላለመቀበል የሚያደርገው ትግል ነው።

ዘሪሁን አሰፋው "የስነፅሁፍ መሰረታዊያን "በተሰኘው መፅሐፍ ሰው  ከማህበረሰቡ ጋር የሚጋጨውን ግጭት እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> ሰው ከማህበረሰቡ ጋር  የሚባለው አንድ ሰው ወይም
>
> ቡድን ከማህበረሰቡ ወግና ልማድ፣ባህል ወይንም የኑሮ
>
> ስነስርዓት ጋር  ሊጋጭ ይችላል።ማህበረሰብ ለረዥም ጊዜ
>
> የኔ ናቸው ብሎ የተቀበላቸው እምነቶች እና የአኗኗር ስርዓቶች
>
> ከግለሰብ ወይም ከቡድኑ አመለካከት እና እምነት ጋር የሚያደርገው
>
> የሀሳብ ሙግትና አለመጣጣም ነው።(2005፣177)

### 2.4.4.5. ሰው ከተፈጥሮ ጋር የመሚየደርገው ግጭት

ሰዉ ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ግጭት የሰው ልጅ ከተለያዩ የተፈጥሮ ክስቶች ወይም ገፅታዎች ጋር የሚጋፈጥበት ነው።ሰዎች ለመኖር ሲሉ በሚያደርጉዋቸው እንቅስቃሴዎችና ተግባር ከተፈጥሮ አካላት ጋር ይጋጫሉ ።ገበሬው ጫካውን መንጥሮ የእርሻ መሬት ሲያዘጋጅ ከጫካው ጋር አካላዊ ግጭት ይፈጥራል። ጫካው በሚመነጠርበት ክስተትም ሰዓትም በጫካው ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትም መጠለያቸው ስለተቆረጠባቸው ከሰው ጋር ግጭት ይፈጥራል።የሰው ልጅ ለእልውናው ሲል ከአካባቢው ልዮ ልዩ ተፈጥሮአዊ ገፅች ጋራ ከእንስሳት፣ከእፅዋት፣ከአየር ጠባይ ከተለያዩ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ጋር የሚያደርገው አለመግባባት ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ግጭት ነው።ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ግጭት

የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ከሆኑ ክስተቶች ከማዕበል፣ከዛፍች፣ከእሾሆች፣ከዝናብ፣ከብርድ፣ከፀሀይ፣ከሙቀትና ከቅዝቃዜ ጋር ፣ከበረሃ ፣ከድርቅ ከረሀብ ጋር የሚደረገው ትግል ነው።

ዘሪሁን አስፋው"የስነፅሁፍ መሠረታዊያን "በተሰኘው መፅሃፍ ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገውን ግጭት እንደሚከተለው አስፍሮታል ።

ሰው ከተፈጥሮ ጋር የሚባለው ግጭት ሰው ለህልውናው ሲል ከአካባቢው ልዩ ልዩ ተፈጥሯዊ ገፅታዎች ጋር የሚያደርገው አካላዊ ግጭት ነው።ሰዎች ከእንስሳት ጋር፣ከእፅዋት ጋር፣ከአየር ንብረት ጋር ይጋጫሉ ።አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ የሚደረግ ግብግብ ነው ።ሰዎች ከእንስሳትና ከአነራዊት ጋርም ይጋጫሉ።አካባቢያቸውን ለህልውናቸው ተስማሚ ለማድረግ በሚያደርጉቸው ጥረቶች ከአሰፈሪና ከጎጂ እንስሳትና አራዊት ጋር ተግል ያካሂዳሉ።እንስሳት እና አራዊቱ የሰውን ህይወት ወይም ሰው እጥቅሙ ላይ የሚያውላቸውን ነገሮች ይካተታሉ።ሁለቱም ገጭቱ ውስጥ የሚገቡበትን ለሚፈልጉትን ነገር ለማሟላት ወይም አላማቸውን ለማሳካት ነው። አካባቢያቸውን ለህልውናቸው ተስማሚ ለማድረግ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ከአስፈሪና ከጎጅ እንስሳትና አራዊት ጋር ትግል ያካሂዳሉ። እንስሳት እና አራዊት የሰውን ህይወት ወይም ሰው ጥቅም ላይ የሚያውላቸው ነገሮች ይተናኮላሉ ሁለቱም ግጭቱ ውስጥ የሚገቡት የሚፈልጉትን ነገር ለማሟላት ወይም አላማቸውን ለማሳካት ነው።( 2005፣175 )

### 2.4.5. መቼት

መቼት ማለት የአንድ ተውኔት ወይም ልብ-ወለድና ጥበባዊ ለሆኑ ፅሁፎች የሚከናወንበት ጊዜ ፣ቦታ እና ማህበራዊ ሁኔታ የሚገልፅበት ነው። መቸት በስነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ ሙሉ የታሪኩን ማህበራዊ ሁኔታ እና የታሪኩን ቦታና መቸ ተደረጉ የሚሉ ፅንስ ሀሳቦችን ከዋናው ታሪክ ውስጥ እነዚህን ተሸክሞ ከታሪኩ ጅማሬ እስከ ፍፃሜ ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን ታሪኩ መቸ እና የት ተፈፀመ የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። መቼት የልቦለዱ አለም ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ታሪኩ የተፈጠረበት ቦታ የተፈፀመበት ጊዜ ሁኔታና በአካባቢው ያለውን ማህበራዊ ሁኔታ የሚያመለክትም ነው መቼትን ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ" በተሰኘው መፅሀፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

መቼት የአንድ ተውኔት ፣የልብ-ወለድ ፣የግጥም እና የፊልም ታሪክ የሚከወንበት ቦታ ፣ጊዜና ማህበራዊ እውነታ ነው። መቼት ሁለት ክፍሎች አሉት ተፈጥሮአዊና ስነ-ፅሁፋዊ(ተውኔታዊ) ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ። የተፈጥሯዊ መቼት በዬብስ ፣በውቂያኖስ፣ሰማይ ላይ የሚደረጉ መልካምድራዊ ትዕይንቶችን እና የጊዜ ክስተቶችን ለምሳሌ የቀንና የሌሊት የበጋና የክረምት መፈራረቆችን ሁሉ ያጠቃልላሉ ተውኔታዊ(ስነፅሁፋዊ ) እንደ ተፈጥሯዊ መቼት ልቅና ግርድፍ ሳይሆን የተመረጠና የተወሰነ አቀራረብ ብቻ ይኖረዋል።( 2009፣11)

#### 2.4.5.1. የመቼት አይነቶች

ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ስለመቼት አይነቶች እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> መቼት ታሪኩ ከሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ ስፋትና ጥበት አንፃር በሁለት ይከፈላሉ። ብዙ ጊዜ በአንድ ተውኔት ፣የልብ-ወለድ፣የመፊልምና የትረካ ስራ ላይ ውስንና አጠቃላይ የመቼት አይነቶች በአንድላይ ተብራርተው ተገልፀው ይቀርባሉ። ይሁን እንጅ አንዳንድ ጊዜ የትኛው አጠቃላይ የትኛው ደግሞ ውስን መቼት እንደሆነ መለየት የሚያስቸግርበት ጊዜ ይፈጠራል። ይህም በሆነ ምክንያት በአንድ የፈጠራ ስራ ውስጥ የነበረው የመቼት አይነት በሌላው የፈጠራ ስራ ውስጥ የነበረው የመቼት አይነት ሆኖ የሚቀርብበት አጋጣሚ ስለሚከሰት ነው።(2009፣14 )

### 2.4.5.2. አጠቃላይ መቼት

አጠቃላይ መቼት ደራሲው በመረጠው የተወሰነ አካባቢ ታሪኩ የሚፈፀምበት ሰፊው እና ትልቁ ጊዜ እና ቦታ ነው። አጠቃላይ የጊዜ መቼት ታሪኩ የሚፈፀምበት ወቅት ፣ አመተ ምህረት ወራት ሊሆን ይችላል። አጠቃላይ የቦታ መቼት ደግሞ ታሪኩ የተከናወነበት ሰፊው ቦታና ትልቁ ቦታ ነው። በአንድ የጥበብ ስራ ውስጥ ሀገር፣ አህጉር፣አለም፣ከተማ ፣ወረዳ የሚገለፅበት የመቼት አይነት አጠቃላይ የቦታ መቼት ነው። አጠቃላይ መቼት የልብ-ወለዱን ታሪክ  መከወኛ ቦታና ጊዜ በስፋት የሚይዝ የመቼት አይነት ነው። ፋንታሁን እንግዳ " የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ አጠቃላይ መቼት እንደሚከተለው አስፍሮታል። አጠቃላይ መቼት በአንድ የተወሰነ ድርሰት  ውስጥ የሚገኘው ትልቁ የድርጊት መከወኛ ፣ የጊዜ መለኪያ እና ትልቁ የድርጊት መከወኛ ቦታ ነው። ለአስረጅነት ያህል ከታሪኩ ጊዜ አኳያ ክፍለ-ዘመኖች፣አመቶች፣ወቅቶች፣ወራቶች፣ሳምንታት ሊሆኑ ይችላሉ። ከታሪኩ ቦታ አንፃር ፕላኔቶች ፣ አህጉሮች፣ ከተማዎች እንደየሁኔታው አጠቃላይ መቼቶች ሆነው ይቀርባሉ። (2009፣15 )

### 2.4.5.3. ውስን መቼት

ውስን መቼት ማለት ቃሉ እንደሚያመለክተው የተወሰነውን የታሪኩን ጊዜ እና የተወሰነውን የታሪኩን ቦታ የሚያካትት ሲሆን የአንድ ድርሰት ታሪክ የሚከናወንበትን ጊዜና ቦታ በአጠቃላይ መቼት ስር ሆኖ ትንሹ ጊዜና እለት ፣ሳምንት፣ስዓት፣ሴኮንድየሚገለፅበት ሲሆን ውስን የቦታ መቼት ደግሞ በአጠቃላይ የቦታ መቼት ስር ያሉትን ሰፈር፣ታክሲ ውስጥ፣መናፈሻ ውስጥ፣መንገድ ዳር፣ቤተ-ክርስቲያን እያለ የአንድን ታሪክ የተወሰነ ቦታ የሚገልፅ የመቼት አይነት ነው። የአጠቃላይ መቼት ቦታ ኢትዮጲያ ከሆነ የውስን መቼት ቦታ አዲስ አበባ፣ናዝሬት፣ጅማ ሊሆን ይችላል። የአጠቃላይ መቼት ጊዜ 2000ዓ.ም ከሆነ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር የውስን መቼት ጊዜ ይሆናል። ውስን መቼት እንዳጠቃላይ መቼቱ ስፋትና ጥበት የሚቀያየር ነው። ፋንታሁን እንግዳ"የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ውስን መቼትን እንደሚከተለው አስፍሮታል። ውስን መቼት በአንድ በተወሰነ ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትንሹ የድርጊት ጊዜና ትንሹ የድርጊት መከናወኛ ቦታ ነው። ለምሳሌ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአንድ ቀበሌ ተወስኖ ታሪኩ የሚከናዎን ተውኔት ብንፅፍ የዚህ ተውኔት ውስን መቼት ከታሪኩ ጊዜ አኳያ ሳምንታት፣ቀናት፣ሰዓታት፣ደቂቃዎች ንጋት፣ምሽት፣እኩለ ቀን፣ ዝናባማ፣ደመናማ ፣ፀሀያማ፣በጠፍ ጨረቃ ሊሆን ይችላል። ከታሪኩ ቦታ አኳያ ሳሎን፣ምኝታ ክፍል፣መፅድ ቤት፣ቅፅረ ግቢ፣ መንገድ ዳር፣የንግድ ማዕከል፣ሊሆን ይችላል።(2009፣15)

### 2.4.6. ጭብጥ

ጭብጥ ማለት ታሪኩ ማስተላለፍ የፈለገው ዋናው ጉዳይ ወይም የልብ-ወለድ ማዕከላዊ ሀሳብ ነው። ጭብጥ ማለት በስነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ የምንፈልገውን መልዕክት ይዞልን ያለው የታሪኩ ቁምነገርን የያዘ የልብ-ወለድ አላባዊያን ነው። ጭብጥ በአንድና በሁለት መስመር ወይም በአረፍተነገር የሚገለፅ የደራሲው መልዕክት ነው። በሌላ አገላለፅ ጭብጥ ደራሲው በፃፈው ታሪክ ውስጥ ትኩረት እንዲሰጠው የፈለገው የታሪኩ ዋና ሃሳብ ነው።

ፋንታሁን እንግዳ" የተውኔት መዝገበ-ቃላትና ብያኔዎቻቸው" በሚለው መፅሀፉ ላይ እንደ ሚከተለው አስፍሮታል።

> *ጭብጥ በስነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ ማለትም በተውኔት በልብ-ወለድ እና በግጥም ፈጠራዎች ውስጥ ማዕከላዊ ወይም ዋና የሚባለው ረቂቅ ሀሳብ ነው። በስነ ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ የሚገኘው ረቂቅ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ተጨባጫዊ በመሆን ጎልቶ የሚወጣው ደራሲው በሚቀርፀው ገፀ-ባህርያትና ድርጊቶቻቸው፣በሚገልፀው መቼት ጥቅም ላይ እንዲውል በሚያደርገው ቋንቋ ውክልና አማካኝነት ነው።( 1993፣112 )*

ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ " በሚለው መፅሀፉ ጭብጥን በሁለት ከፍሎ ይመለከተዋል።

> አንድ ፅሁፍ አብይ ወይም አውራ ጭብጥ እንደሚኖረው ባያጠራጥርም ከቁጥር አንፃር ከአንድ በላይ ንዑሳን ጭብጦች ሊኖሩት እንደሚችሉ ማወቅ ይገባል። ለምሳሌ እያነበብነው ያለነው ተውኔት ሦስት ገቢሮችና አስር ትዕይንቶች ቢኖሩት እያንዳንዱ ገቢርና ትዕይንት አንፃራዊ የሆነ የራሱ የሆነ ምሉዕነት ያለው ታሪክ ስለሚኖረው በነዚህ ቁጥሮች ልክ ቁርጥራጭ ጭብጦችን ልናገኝ እንችላለን። ይሁን እንጅ ታዲያ ሁሉም ገቢሮችና ትዕይንቶች በአንድ በሚገጣጠሙ ጊዜ አንድ ጎልቶ የሚታይ ማዕከላዊ ጭብጥና ብዙ ንዑሳን ጭብጦች ያስገኙልናል።(2009፣61 )

*አብይ ጭብጥ ማለት የአንድ ጥበባዊ ፅሁፍ ታሪክ በዋናነት ሊያንላው ወይም ሊያስተላልፈው የፈለገው ነገር ሲሆን ንዑስ ጭብጥ ደግሞ በአብይ ጭብጡ ሰር የሚከናወኑ ትንንሽ ክስተቶችን የያዘ ነው። እነዚህ አብይና ንዑስ ጭብጦች በአንድ ስነ-ፅሁፍ ላይ የተከናወኑ ደራሲው እንዲታወቅለት የሚፈልጋቸውን ሀሳቦች የያዙ ሲሆኑ በአንድ ላይ ታሪኩን ወደ ፊት የሚያራምዱ ናቸው።ጭብጥን*

*ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ በሁለት ከፍሎ አካባቢያዊ እና ሁንተናዊ ጭብጥ ብሎ ይመለከተዋል።ጠቅለል ባለ መልኩ ጭብጥ ግለኛ ወይም አካባቢያዊ ጭብጥ ቀሚሉ ሁለት አብይ ክፍሎች ይከፈላሉ። (2009፣62)*

### 2.4.6.1. አካባቢያዊ ጭብጥ

አካባቢያዊ ጭብጥ ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚከወኑ ድርጊቶችን የሚይዝ ጊዜና ዘመን ሲቀያየር ትምህርቱ የሚለዋወጥ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ብቻ ግንኙነት ያለው ታሪኩ የተፈፀመበትን ሁኔታዎች ብቻ የሚያንፀባርቅ ሲሆን ዘመኑ ሲቀየር ታሪኩም አብሮ የሚቀየርና ትርጉም የማይሰጥ ይሆናል። ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ አካባቢያዊ ጭብጥ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

*አካባቢያዊ ጭብጥ በአንድ ማህበረሰብ የሚከሰተውን ወቅታዊ ፣ሰነ-መንግስታዊ፣ማህበራዊ፣ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴወችን መሠረት ያደረገ መልዕክት ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የማያረጅ የማያፈጅ መሆኑ አያጠራጥርም። አካባቢያዊ ጭብጥ ላንድ ለተወሰነ ማህበረሰብ ትኩረት አድርጎ ስለሚፃፍ ተደናቂነቱ ጊዜያዊ ነው ። ለምሳሌ በሀገራችን ከተፃፉት ተውኔቶች መካከል የአውሬዎች ተረት "ፋቡላ" የተባለው የበጅሮንድ ተክለ ሃዋሪያት ተክለ ማርያም ተውኔት ጭብጥ ግላዊ ወይም አካባቢያዊ ነው ። ታሪኩ የተፈፀመውም የልጅ እያሱን አስተዳደር ለመውቀስ ነበር። የዚህ ተውኔት ጭብጥ ታዲያ አካባቢያዊ በመሆኑ ለምንገኝበት ዘመን ተደራሲ በታሪካዊነቱ ካልሆነ በወቅታዊ ፓለቲካ ይዘቱ የሚሰጠው ትርጉም የደበዘዘ ነው።(2009፣63)*

### 2.4.6.2. ሁለንተናዊ ጭብጥ

ሁለንተናዊ ጭብጥ ለአንድ ዘመንና ለተወሰነ ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ለማነኛውም ዘመንና ማህበረሰብ እንዲጠቀም ታስቦ የሚፃፍ ታሪክ ነው። ሁለንተናዊ ጭብጥ ሀገርና ድንበር የማይወስነው ሁሉም ቦታ አንድ አይነት ትርጉም የሚሰጥ ሁሉንም ሰዎች የሚያሳትፍ ከትውልድ ትውልድ ከዘመን ዘመን እንኳን ቢቀያየር እንኳን ትርጉሙ የማይቀያየር የጭብጥ አይነት ነው። ስለሁለንተናዊ ጭብጥ ፋንታሁን እንግዳ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ " በተሰኘው መፅሀፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል ።ሁለንተናዊ ጭብጥ

ያለው ተውኔት ወይም የስነ- ፅሁፍ ስራ በአንባሩ መሰረታዊ በሆኑ በሰው ልጅ ምኞቶች፣ተስፋዎችና አውዶች ላይ ስለሚመሠረት ለየትኛውም ድርጊቶቻቸው በሚገባ የሚገልፅና ለየትኛውም ማህበረሰብና ለቀጣዮችም ዘመናት የሚስማማና ግቡነት ያለው ነው።(2009፣6)

### 2.4.7. አንባር

አንባር የልብ-ወለዱን ታሪክ የሚተርከው ወይም የሚያቀርበው ማን ነው? የልቦለዱን ታሪክ የሚያቀርበው ሰው ከልብ-ወለዱ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? የልብ-ወለዱን ታሪክ የተረከው ከምን አኳያ ነው? ሚለውን ሀሳብ የያዘ ሲሆን በደራሲና ባንባቢው መካከል ሆኖ ሁኔታዎችን የሚገልፅና የሚተረጉም የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ ለአንባቢያን የሚተርክ ነው። አንዳንዴ ስለ ገፀ-ባህርያቱ ስሜትና ፍላጎት ትችትና ፍርድም ይሰጣል። ዘሪሁን ስፋው "የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን " በተሰኘው መፅሀፉ አንባርን በአራት ከፍሎ ይመለከተዋል። "ሁሉን አዎቅ፣ውስን አዎቅ አንባር፣አንደኛ መደብ አንባር እና ተውኔታዊ አንባር " ብሎ ይከፋፍላቸዋል።(2005፣191)ዘሪሁን አስፋው" የስነ-ፅሁፍ መሠረታዊያን" በሚለው መፅሀፉ አንባርን እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> አንባር ማነኛውም ልብ-ወለድ በደራሲውና በአንባቢው መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልፅና የሚተረጉም አልፎ አልፎም በግልፅ አብዛኛውን ጊዜ ግን በውስጠ አዋቂ የሚኖር የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርበው ተራኪ ነው። ተራኪው ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፊ ወይም ታሪኩ የማይመለከተው ታዛቢ ሊሆን ይችላል። ተሳታፊ ከሆነ ታሪኩ የሱም ታሪክ በመሆኑ የራሱንም ሆነ ከሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ገፀ-ባህርያት ታሪክ በሱው አመለካከት ያቀርባል። ታዛቢ ከሆነ ደግሞ ዳር ቆሞ ያየውን እና የታዘበውን እንዳለ ነው የሚያቀርበው። አንዳንዱ ተራኪ የገፀ-ባህሪያቱን ልዩ ልዩ ድርጊቶችና አጠቃላይ አኗኗር በሚገባ በማወቁ አንድም ሳይቀር ለአንባቢያን ያቀርባል። አንዳንዱ ደግሞ እውቀቱ የተወሰነ ይሆንና ስለሁሉም መተረክ አይችልም። ሌላው ደግሞ በገፀ-ባህሪያቱ ሳይገባ እራሳቸው ማንነታቸውን እንዲያሳዩ ያደርጋል። ደራሲያን መርጠው የልብ-ወለዳቸውን ታሪክ የሚያቀርቡባቸው አራት መሠረታዊ የአንባር አይነቶች መኖራቸው ይታወቃል። እነሱም ሁሉን አወቅ አንባር፣ውስን ሁሉን አወቅ አንባር፣አንደኛ መደብ አንባርና ተውኔታዊ አንባር ተብለው ይጠራሉ። (2005፣190)

### 2.4.7.1. ሁሉን አዎቅ አንፃር

ሁሉን አዎቅ አንፃር የልብ-ወለዱን ታሪክ ያለገደብ በነፃነት የሚተርክ  የገፀ ባህርያቱን ልዩ ልዩ ስሜቶች የሚያውቅና የሚያወጣ እያንዳንዱን ሀሳብ መገምገምና ትችት መስጠት የሚችል የራሱን እምነትና ፍልስፍና በሰፊው የማንፀባረቅ መብት ያለው ነው። ሁሉን አወቅ አንፃር ታሪኩን የሚተርከው በሦስተኛ መደብ እሱ፣እሷ ፣ እነርሱ እያለ ሁሉንም ነገር ዝርግፍ አድርጎ የሚያቀርብ ስለሆነ አንባቢያን እንዲመራመሩና የገ-ፀባህሪያቱን ማንነት በራሳቸው እንዲያውቁ የሚያስችል የአንፃር አይነት ነው።

ዘሪሁን አስፋው " የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊን " በተሰኘው መፅሀፉ ሁሉን አዎቅ አንፃርን እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> ሁሉን አወቅ አንፃር ለተራኪው ሰፊ ነፃነት የሚሰጥ በሶስተኛ መደብ የሚተረክ የትረካ አንፃር ነው። ቃሉ እንደሚያመለክተው ተራኪው በልብ-ወለዱ ውስጥ የሚከናወን ሁሉ የገፀ-ባህርያቱን ማንነት ፣ ስሜትና ሀሳብ፣ምኞትና ፍላጎት በሚገባ ያውቃል። ገፀ-ባህሪያቱ በልብ-ወለድ ህይወታቸው የሚገጥማቸውን እጣፈንታ በውል የተገነዘበና ሚስጥራቸውን በዝርዝር የሚያውቅ በመሆኑ ገመናቸውን አውጥቶ በግልፅ የማሳየት አቅም አለው።(2005፣191)

### 2.4.7.2. ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር

ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር የገፀ-ባህርያቱን ምኞትና ፍላጎት የሚያውቅ ፣የራሱን እምነትና አስተሳሰብ የማራመድ ስልጣን የሌለው ፣አስተያየትና ትችት የማወቅና የማቅረብ ነፃነት የሌለው ፣ የሚሰማውን ብቻ ከዋናው ገፀ-ባህሪ አኳያ ብቻ የሚተርክ፣ዋናው ገፀ-ባህሪ ከሚናገረው ታሪክ ውጭ የሚናገረው ታሪክ የሌለው እና ውስን ታሪኮችን ብቻ የሚያውቅ የአንፃር አይነት ነው። ዘሪሁን አስፋው" የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን " በተሰኘው መፅሀፉ ውስን ሁሉን አወቅ አንፃርን እንደሚከተለው አስፍሮታል።

ውስን ሁሉን አወቅ አንፃር እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር በሶስተኛ መደብ የሚተርክ ሲሆን ተራኪው የሁሉንም ገፀ-ባህርያት ስሜት አስተሳሰብም ሆነ ፍላጎት አያውቅም። የራሱንም ፍልስፍና አስተያየት የመንዛት አቅሙ የተገደበ ነው። ብቻ የሚያየውንና የሚሰማውን ከተወሰኑ ገፀ-ባህርያት አንፃር ያቀርባል። በዚህ አንፃር የሚተረክ ትረካ በአብዛኛው ከዋናው ገፀ-ባህሪ አኳያ ነው የሚተረከው። (2005፣1994)

### 2.4.7.3. አንደኛ መደብ አንፃር

አንደኛ መደብ አንፃር በልብ-ወለዱ ውስጥ የተለያዩ ታሪኮች እኔ አየሁ እንደዚህ ተፈጠረ እነዘያለ በታሪኩ ውስጥ ያሉ እያንዳንዳቸውን ትንንሽም ሀሳቦችና ድርጊቶች እና ስሜቶች የሚገልፅ የአንፃር አይነት ነው። ዘሪሁን አስፋው"የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን" በተሰኘው መፅሀፉ ስለ አንደኛ መደብ አንፃር እንደሚከተለው አስፍሮታል። ተረረኪው "እኔ" ይህን አየሁ ይህን ተመለከትሁ እገሌ የሚባለው ገፀ-ባህሪ በዚህ ወረደ በዚህ ወጣ ፣እገሌ ደግሞ እንዲህ ያለ ችግር ደረሰበት ፣እገሌና እገሌ ተፋቀሩ፣ተጣሉ ወይም በራሴ ላይ እንደዚህ አይነት ድርጊት ተፈፀመብኝ እንተናን ወደድሁ ወይም ጠላሁ ወዘተ... እያለ የሚተርክ የአንፃር አይነት ነው። (2005፣196)

### 2.4.7.4. ተውኔታዊ አንፃር

ተውኔታዊ አንፃር ፊት ለፊት የሚያየውን የገፀ-ባህርያቱ ታሪክ እና ስሜት ሳይጨምር ሳይቀንስ የሚያቀርብ የአንፃር አይነት ነዉ ። ተውኔታዊ አንፃር በገፀ-ባህርያቱ የሚያወሩትን የሚሰማውንና የራሱን ሀሳብ የመግለፅ መብት የለውም ። ምክንያቱም ተውኔታዊ አንፃር በገፀ-ባህርያቱ ስሜትም ሆነ ድርጊት አስተያየትና ትችት መስጠት ስለማይችል ።

ዘሪሁን አስፋው " የስነ-ፅሁፍ መሠረታዊያን" በተሰኘው መፅሀፉ ተውኔታዊ አንፃርን እንደሚከተለው አስፍሮታል።

> ተውኔታዊ አንፃር ተራኪው በገፀ-ባህርያቱ ድርጊትም ሆነ በሁነቶች ምንም አይነት አስተያየት የማይሰጥ የአንፃር አይነት ነው። በታሪኩ ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶችም ሆኑ የገፀ-ባህርያቱ ግንኙነቶች ወይም የሚግባቡባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ነው የሚቀርቡት። (2005፣200)

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.1. የተልሚድ እረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ

በደራሲ ይስማከወርቁ ተደርሶ በ2005 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ በኤች ዋይ ማተሚያ ቤት ታትሞ የወጣው ተልሚድ ረጅም ልቦለድ በ50 ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በውስጡም192 ገፆችን የያዘ ነው። ታሪኩም የሚከተለውን ይመስላል።

ታሪኩ የሚጀምረው ተልሚድ በመኪና ተገጭቶ ፍቅረኛው ፀዳይ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስታሳክመውና ቀኝ እጁን ተቆርጦ ከሰመመን ሲነቃ ነው ። ተልሚድ እስከ 1982 ዓ.ም የኢትዮጵያ የመከለያ ሰራዊት አባል የነበረ ሲሆን በወቅቱም የደርግ ሰራዊት በኢህአዴግ ጦር ከተሸነፈ በኋላ የደርግ ወታደሮች ሲበታተኑ ጠመንጃ ውስጥ ጥይቶችን በአሮጌ መፅሐፍ ለውጦ በባቡር በመሳፈር በጅቡቲ በኩል በማለፍ ወደ ማዳጋስካር ተሰደደ ። ማዳጋስካር በሚኖርበት ጊዜ በከተማው "ዜቦ" በመባል የሚታዎቁ በሬዎችን በመጠበቅ ይተዳደራል ። ከዚህ ስራው በመላቀቅም መርከብ በማፅዳት ተቀጥሮ ሲሰራ ከመርከቡ ጋር ወደ ግሪክ ያመራል። ግሪክ ሀገር አንድ በስደተኞች ህይወት ያተኮረ ድርሰት የምትፅፍ አኒያና የምትባል ደራሲ ጋር ይተዋወቃል ። አኒያና ለተልሚድ በግሪክ ሀገር የስራ ፈቃድ በማውጣት በቤት ውስጥ ውሾችን እንዲያረባ እና እንዲንከባከብ አደረገችው። ተልሚድ የድርሰት ፅሁፍ ፍላጎት ስለነበረው ደራሲ አኒያን የምትፅፈውን እያየ ማስተካከያ ይሰጣል ። አኒያና የተልሚድን ልቦለድ " chapter of may life " በሚል ዕርስ ሲጀመር የመፅፉን ጥቂት ምዕራፎች አንብባ በጣም በመደሰቷ እንዲጨርሰው ገንዘብ በመስጠት ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ላከችው። ተልሚድ ወደ ሀገሩ ሲመለስ እናቱ የምትኖርበትን ቤት ቢገኘውም እናቱን ግን ያጣታል ። በግቢው ውስጥ የሚኖረው ዝንመሪቅ እናቱ እንደሌሉ እና በኢትዮጵያ እና በኤርትራ ጦርነት ወቅት ወደ ኤርትራ እንደተሰደዱ ይነግረዋል። ዝንመሪቅ የግቢው ባለቤት እሱ እንደሆነና የቤት ቁልፍ ይሰጠዋል ። ተልሚድም ሌላ መሄጃ ስሌለው እናቱን በማጣቱ እያዘነ ወደ አደረገበት ቤት ገብቶ መኖር ይጀመራል ። ከግቢው በሚያድርበት ወቅት ከዝንመሪቅ እና ከብሩክታይት ልጅ ከፀዳይ ጋር ይተዋወቃል ። ፀዳይ በስነፅሁፍ የመጀመሪያ ድግሪዋን ያገኘች ስትሆን "ማርዳራ"የተባለ የነርብ በሽታ የተጠቃች ሴት ናት። በሽተውም ነርቮቿን በማዳከም ወደ እብደት የሚያደርስ እንደሆነ የኩባ ሀኪሞች ነግረዋታል። መዳኒቱም በቀን ሁለት ጊዜ በጭንቀት  እና በወጥረት ያልተሞላ ወሲብ መፈፀም ነው ። በዚህም ሁኔታ እያለች ቀስበቀስ ተልሚድ ጋር በመግባባት አብረው መዋል ማደር ሲጀምሩ ፍቅር ይይዛቸውና ፍቅረኛሞች ይሆናሉ። በዚህ ጊዜ በሽታዋ መድሀኒት እንደሌለው ለተልሚድ ትነግራቸዋለች ። በአንድ ምሽት ተልሚድ

እና ፀዳይ በከተማው ሲጓዙ ተልሚድን አንድ መኪና አባሮ ይገጨዋል ።መኪናው ሲገጨውም በመጎዳቱ ምክንያት ሆስፒታል ገብቶ የቀኝ እጁ እንዲቆረጥ ተደረገ ። በመኪና እንዲገጭ ያደረገውም የፀዳይ አባት ዝንመሪቅ ነው ። ዝንመሪቅ ለገንዘብ ትልቅ ፍቅር ያለውና ያለፋበትን መውሰድ የቆመ ሲሆን ሰውን በገንዘብ የሚለውጥ ሰው ነው። ብርሩክታዊት በልጇ ህመም ትኩረት ሰጥቶ ስላልተንከባከባት እና ስላላሳከማት ያላትን ንብረት መክፈል እንደምትከፍል ስትነግረው ገንዘቡን እንድትከፍለው ተልሚድን እንዲገድላት እና ሀብቱን ብቻዋን እንዲጠቀም ለተልሚድም ከገደለላት ገንዘብ እንደሚሰጠው ይነግረዋል ። ተልሚድም በሀሳቡ እንደማይስማማ ይነግረዋል ። በዚህ ምክንያት ነው ሚስጥሩ እንዳይሰማ ለማድረግ ዝንመሪቅ ተልሚድን በመኪና ያስገጨው ።ዝንመሪቅ ከዶክተር ጌዲወን ጋር በመመሳጠር ብሩክታዊትን ያሰበችውን እንታሳካና አፏን አፍኖ ያበደች በማስመሰል አማኑኤል ሆስፒታል ይወስዳታል። የእእናቷን አማኑኤል መግባት ያልሰማችው ፀዳይ ተልሚድን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እያስታመመች ነበር ። ተልሚድን በመኪና የገጩት ሰዎች እየተከታተሏቸው መሆናቸውን ሲያውቁ ከሆስፒታሉ ወጡ። ወደ ቤታቸው ሲሄዱም ዘበኛው አላስገባም ይላቸዋል ። ዘበኛውን አስገድደው በመግባት ሁሉንም ነገር ይነግራቸዋል። ብሩክታዊት ያለችበትን ግን ሳያውቁ ይወጣሉ። ዝንመሪቅ ከቻይና ሀገር የኮንትሮባንድ ሳልባጅና ጥይት የማያስመቱ ልብሶችን ወደ ሀገር ቤት በማስገባት ሲጣድፍ ቆይቶ እቃውን ወደ ኢትዮጵያ በመርከብ ልኮ እሱ በአውሮፕላን በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት እቃውን ይጠባበቃል። ፀዳይና ተልሚድ ሳልባጁን ለመያዝ እና እናቷን ለመፈለግ ወደ ድሬዳዋ ይሄዳሉ ።በመጨረሻም ስጡል የተባለው የፀዳይ አጎት የብሩክታዊት ወንድም ከቻይና ሀገር በመምጣት ስልክ በመደዋወል ከፀዳይ እና ተልሚድ ጋር ይገናኛሉ ። የተፈፀመውን ሁሉ ይነግሩታል ። በመጨረሻም የዝንመሪቅን ኮንትሮባንድ እቃ በቁጥጥር ስር ያውለዋል። አማኑኤል ሆስፒታል ሲሄዱም ብሩክታዊት በተሰጣት መድሀኒት አብዳ የገኘታል። ፀዳይም እናቷ አብዳ ስታገኛትም በጣም ታዝናለች ። ከዚያም ተልሚድ ፀዳይ እና ብጡል አንድ ላይ ወደ ዝንመሪቅ ቤት በመሄድ ዝንመሪቅን ከሦስት ተከታዮች ጋር በማፈን ይገድሏቸዋል ። ፀዳይም በሽታዋ ተነስቶባት ዝልፍል ብላ ትወድቃለች ።በሽታዋም እየተባባሰባት በመሄዱ ተልሚድ ለአራት ወራት ያክል ከፖሊስ እየተደበቀ አስታመማት። በመጨረሻም ፀዳይ አልሻላት ሲል ትሞታለች ተልሚድ እና ብጡል ሳጥን አዘጋጅተው መቃብር ቆፍረው በአንድ ሌሊት የፀዳይን አስከሬን በአንድ መኪና ጭነው ወደ መቃብር ቦታ ይዘዋት ይሄዳሉ ። ተልሚድ ከአረቂ ጋር መርዝ በመቀላቀል እራሱን ለማጥፋት የጠጣል። የፀዳይን አስከሬን በቀኝ እጁ አንቆ ደረቱ ላይ በመለጠፍ ትንሽ ተፈረጋግጦ እሱም ከፀዳይ ጋር አብሮ ይወድቃል ። የፀዳይ አጎት ብጡል በሁኔታው እያዘነ እና እያለቀሰ የሁለቱን ጥንድ አስከሬን እየዳሰሰ ታሪኩ ይፈፅማል ።

### 3.2. "የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ከልበ- ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና

#### 3.2.1. የተልሚድ ልበ-ወለድ ታሪክ

የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ታሪክ በምዕራፍ ሁለት ስለ ታሪክ ማየት አንደተሞከረው ደራሲው በመሠጠው ማህበረሰብ ጊዜ እና ቦታ በቅደም ተከተሉ መሰረት የታሪኩን ቁርኝነት አንዱ ታሪክ ለአንዱ ታሪክ ያለውን ይተርካል ። "የተልሚድ" ረጅም ልቦለድ ታሪክ መጀመሪያ ፣ መሀከል እና መጨረሻ ያለው አንዱ ለአንዱ የተሳሰረ ሰንሰለት ያለው እስኪመስል ድረስ በዝምድና በፍቅር እና በጋብቻ ግምዶሽ ያለው ነው ። "የተልሚድ" ረጅም ልቦልድ ማሚለት ያለበትን የተለያዩ ታሪኮችን የተለጣጠፈ የታሪክ ሂደቶችን ያሚላ ነው። ታሪኩም ገፀባህርይያቱም አንዳቸው ለአንዳቸው ያላቸውን ፍቅርና መተሳሰብ በሌላ በኩል ደግሞ በዝንመሪቅ ክፋት እና ተንኮል የሚያሰፋ ሲሆን የብሩክታዊትን ደግነት እና የእናትነት ፍቅር ያሳያል። በተልሚድ እና በፀዳይ መካከል ስላላቸው ፍቅር እና አንዳቸው ለአንዳቸው መተሳሰባቸውን ያሳያል ። "ተልሚድ" ረጅም ልቦለድ ታሪክ ልቦለድ ታሪክ ልቦለድ ላይ ያሉትን ልዩ ለዩ የሰው ልጆች ባበብርያት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ። "የተልሚድ" ልቦለድ ከቻይና እስከ ኢትዮጵያ ከማዳጋስካር እስከ ግሪክ ከብጡል ቤት ቻይና እስከ ዝንመሪቅ ቤት አዲስአበባ ከዛም ከነብጡል የትውልድ ቦታ ድሬደዋ ድረስ በምናብ የሚያስጉዘን ሲሆን የዝንመሪቅን ለገንዘብ ብሎ የሚስቱን የልጁን የተልሚድንና የእናቱን ህይወት ሲያበላሽ እና እነሱም ከዚያ ችግር ለመውጣት ህይወት በልዩ ልዩ መንገድ የጋረጠችባቸውን ፈተናዎች ለማሸነፍ ገፀባህርያቱ በየፊናው ሲፍጨረጨሩ ያሳያል ። "የተልሚድ" ረጅም ልቦለድ ታሪክ እንደ ታሪክ ማሚላት ያለበትን የነገሮች ቅደም ተከተል በገፀባህሪያቱ የሚፈፀሙትን ድርጊቶች አነሳስ አፈፃፀም እና የመጨረሻ ውጤትን ለአንባብያን አድርሷል ።

#### 3.2.2. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ትልም

የተልሚድ ረጅም ልቦለድ በምዕራፍ ሁለት ለማየት እንደተሞከረው ልበ-ወለድ ውስጥ ምን ? ለምን ?ተደረገ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘውን መልስ የሚያካትት ነው። ተልሚድ ረጅም በምክንያትና ከዛ ቀጥሎ በሚመጣው ውጤት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። ለዚህም ማስረጃ ዝንመሪቅ እና ተልሚድ ያደረጉትን ንግግር እንመለከታለን ።

"ቃልቲ መግባት ካለብህ ብሩክታዊትን ግደልልኝ እና ግባ ብሩክታዊትን ከአንድ ቅማላም ሰራተኛ ጋር ተወዳጅታ ያለኝን ሁሉ ልታሳጣኝ እንዳሰበች ደረሽባታለሁ። ልትፈታኝና ሀብቴን ሁሉ ልታሳጣኝ

ብትችልም የኔን እጆች ለሰንሰለት ዳርጋ ወህኒ ቤት የምገባበትን መንገድ እያዘጋጀችልኝ እንደሆነ ደርሸባታለሁ። ሳትቀድመኝ ለምን አትቀድምልኝም"( ገፅ ፣140)

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው የብሩክታዊት ፍች መፈለጓ ዝንመሪቅ ሊገላት እንዳሰበ እና በመጨረሻም አማኑኤል አዕምሮ ህመማን ሆስፒታል እንድትገባ ምክንያት ሆኗታል ። አማኑኤል መግባቷም የእብዶች እብደት ተጋብቶባት እንድታብድ ምክንያት ሆኗታል። ተልሚድም የእኔን ሚስጥር መስማቱ የግድያ ሙከራ እንዳደረገበት እና በመኪና ተገጭቶ ቀኝ እጁን እንዲያጣ ምክንያት ሆኖታል ። ትልም በምክንያት እና በውጤት የተመሰረተ ስለሆነ ተልሚድ ረጅም ልቦለድ ምን ? ለምን ? ተደረገ ከዛስ ምን ውጤት አስገኘ የሚለውን ያመለክታል ። የተልሚድ ረጅም ልቦለድ ትልም መግቢያ መህከል እና እና መደምደሚያ ያለው ልቦለድ ነው። በመግቢያው ላይ ገፀባህርይያቱን ያስተዋውቀናል መህከል ላይ አላማቸውንና ለአላማቸው መሳካት የሚያደርጉትን ትግል ያሳያል። የመጨረሻ ወይም መደምደምያ ሁሉም ገፀባህሪያት እንደፍላጐታቸው ሳይሆን ሲቀር እና እንደየ ስራቸው ፍፃሜዎቻቸውን ያገኛሉ። ለምሳሌ ዝንመሪቅ ሚስቱን ስታብድ ለገንዘብ ብሎ አማኑኤል ሆስፒታል ስላስገባት በሰዎች ላይ የአካል ማጉደልና የነፍስ ማጥፋት ጥቃት ስለሚያደርስ እሱም በሰው እጅ ህይዎቱ በሰው እጅ ህይዎቱ አልፏል። በዚህ የታሪክ ሂደት እንደምንመለከተው አንድ የልቦለድ ትልም ማሟላት ያለበትን ምክንያትና ውጤት ተልሚድ ልቦለድ አሟልቶ ተመልክተናል ።

### 3.2.3. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ገፀ-ፀባህርያት አሰሳል

ተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ አምስት ዋነ ዋና ገፀባህርይት ሲኖሩት አራት አስተኔ ገፀ-ባህርያትን ያካተተ ነው።

#### 3.2.3.1. የተልሚድ አካላዊ አሰሳል

ረጅም ጠይም ጎልማሳ በሚባለው የእድሜ ክልል የሚገኝ በደረሰበት የመኪና አደጋ ቀኝ እጁ የተቆረጠበት ወታደራዊ የሆነ አቋም ያለው ነው። ለማስረጃነትም ከመፃፉ ለመግለፅ የተሞከረው እንደሚከተለው ነው ።

"ፀዳይ ለተልሚድ ይስማማዋል ብላ ያሰበችውን ነጭ ሙሉ ሱፍ በእርግጥ በልኩ እንደተሰራ ሁኖ አምሮበታል ። ፈገግ ብላ ስትመለከተው ከቆየች በኋላ አምሮብሀል መልአክ መስለሀል ስትለው በአይኑ ተዎርውሮ ከቀኝ እጁ ላይ አረፈ አንድ እጅ ብቻ ያለው መልአክ ተልሚድ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮህባት። "(ገፅ ፣68)

ከእነዚህ ንግግሮች እንደምንረዳው ተልሚድ የሚያምር አቋም ያለው ሱፍ ሲለብስ የሚያምርበት ግን ቀኝ እጁ የተቆረጠ እንደሆነ ያስረዳናል።

### 3.2.3.2. የተልሚድ ማህበራዊ አሰሳል

ተልሚድ እስከ 1983 ዓ.ም ማለትም ወታደራዊ መንንግስትደርግ እስከሚወድቅበት ጊዜየኢትዮጵያ መከለል ሰራዊት ሆኖ ያገለገለ ሲሆን አባቱም በሶማሊያ ጦርነት ስለሞቱ እናቱ ብቻቼውን ያሳደጉት ነው። ማስረጃማስረጃነትም ከመፃሀፉ የሚከተሉትን ንግግሮች እንመለከታለን።

"ተልሚድ ሁሉን ነገር ለማስታወስ ሲሞክር ትውስታው እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል እንደነበር እስታውስ ። ግንቦት 17 2983 ዓ.ም አረንጓዴ በለበሱ የደርግ ወታደሮች አዲስ አበባ ያለመሰላውን መሳል ነበር ።"(ገፅ፣10)

ተልሚድ የደርግ ስርዓት ከወደቀ በኋላ ሚስትም ሳያገባ ወደ ሀገሩም ሳይመለስ ወደ ማዳጋስካር ሄዶ "ዜቦ"በመባል የሚታዎቁ በመጠበቅ ይተዳደር ነበር ።

" የኢትዮጲያ መከላከያ ሰራዊት የነበረ ሲሆን በወቅቱም የደርግ ወታደር በኢህአዴግ ጦር ከተሸነፈ በኋላ የደርግ ወታደሮች ሲበተኑ ጠመንጃና ጥይቶችን በአሮጌ መፅሐፍ ለውጦ በባር ተሳፍሮ በጅቡቲ በኩል በማለፍ ወደ ማዳጋስካር ተሰደደ። ማዳጋስካር በሚኖርበት ጊዜ በከተማው በማፅዳት እና "ዜቦ" በመባል የሚታዎቁ በሬዎችን በመጠበቅ ይተዳደር ነበር ። ከዚህ ስራው በመልቀቅም መርከብ በማፅዳት ተቀጥሮ ሲሰራ ከመርከቡ ጋር ወደ ግሪክ ያመራል ። "(ገፅ፣78)

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ተልሚድ ያላገባ እና ቋሚ ስራ እንደሌለው በየጊዜው የማቀያየሩ ስራዎችን እንደሰራ እና የደርግ ወታደር እንደነበር ይገልፃል ።

### 3.2.3.3. የተልሚድ ስነ-ልቦናዊ አሰሳል

ተልሚድ ሀሳብ እና ምኞቱን ለማሳካት የደራሲነቱን ውጥን ጥግ ለማድረስ ከግሪክ ማዳጋስካር ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ የተንከራተተ እና ብዙ ችግርን ያሳለፈ ነው ። ተልሚድ ክፋት እና ተንኮል የሌለበት አፍቃሪ ልብ ያለው ነው። ተልሚድ ።ራሲ የመሆን ህልም እና ምኞት ያለው ሲሆን ለማስረጃነትም ከመፅሃፉ ላይ ተልሚድ ከዠንመሪቅ ጋር ያደረገውን ንግግር እንመለከታለን።

"ለምን ብዙ መኖር እንደምፈልግ ታውቃለህ ብዙ ምኞትና ፍላጎቴን ሳላሳካ መሞት ስለማልፈልግ ነው ። እኔ በጥበቅ የምፈልገው ህይወቴን በሙሉ ለሳካት የማስበት ምኞት አለች ገርንመሪቅ ተልሚድን አቋረጠው "

"ጥበቋ ነገር ምንድን ናት"

"ስነፅሁፍ !"

"አዬ ጉድ ! እናንተ ፀሀፊዎች ስትባሉ ዙራችሁ ዙራችሁ ከዚች አትዎጡም ታዲያ እኔ ምን ላግዝህ ?ነጭ ወረቀት አጣህ ?"

"ነጭ ወረቀት አጥቸ ያልፃፍኩት ያልፃፍኩት ሀሳብ ውስጤ የለም ። ግን....."

"ሴት አስፈለገህ ? .....እራብህን እያሻሻችልህ .....ቂቂቂቂቂ..."

"እየቀለድሁ አደለም !"

"እና የሚያስፈልግህን አትናገርም?"

"ስሜት ነው የሚያጥረኝ ስሜት !የስነፅሁፍ ሰው ልክ እንደእርጉዝ ነው ። የማያምረው ነገር የለም ።"

"ቂቂቂ.....ምን ብዙ ሴቶች ከበውህ እነሱ ስሜትህን ሊቀሰስቅሱልህ ይችሉ ይሁን ?..."

"እርግጥ እንዳልከው የሴቶች ረጃጅም ጣቶች የሚቀሰቀሱት ስሜትም ይኖራል ።የኔ ስሜት ግን ፀጥ ያለ ሰው የሌለበት ባዶ ክፍል ነው የሚቀሰቅሰው ።(ገፅ፣127)

ከእነዚህ ንግግሮች እንደምንረዳው  ተልሚድ ለስነፅሁፍ ትልቅ ቦታ ያለው ለስነፅሁፍ ሲልም የማይከፍለው መስዋዕትነት እንደሌለ ነው ።

3.2.3.4. የተልሚድ ሞራላዊ አሰሳል

ተልሚድ መልካም መልካም ስነምግባር ያለው ሰው የሚያከብር ሰው የሚረዳ ከገንዘብ ይልቅ ሰውን የሚያስቀድም ነው ። ከመፅሀፍም ላይ ሀመፃፍያ ቦታ እንዲሰጠውና እንዲረዳው ብሩክታዊትን እንዲገልለት ቢጠይቀውም ለጥቅሙ ሲል ሰው እንደማይገድል ሲገልፅ እንመለከታለን ፦

"ስማኝ ከልብህ እንዳግዝህ ትፈልጋለህ ?"

"አዎ! ድርሰቴን ቁጭ ብየ በተረጋጋ መንፈስ መፀሀፍያ ወይም ማረፊያ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ።"

"አትቀልድ እኔ ከምሬ ነው ።"

"ጥሩ! የምልህን ትፈፅማለህ ! ከነገርሁህ በኋላ ወደኋላ መሸሽ የለም ።"

"አልሸሽም"

"ብሩክታዉትን ከገደልህልኝ ሁሉን አሟላልሀለሁ።"

አልችልም ብሩክታዊትን የሚያንቅ የሚዘረጋ እጅ አይኖረኝም ።ይቅርታ  አድርግልኝ ጋሼ ይህን ማድረግ አልቻልም ። ይህን ሃሳብህን ወዲያ አስገባው ብትመለስ ይሻላል ።"(ገፅ፣140)

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ተልሚድ ምንም አይነት ችግር ውስጥ ቢሆን ሰው የሚጎዳ ነገረር እንደማያደርግና መልካም አስተሳሰብ እንዳለው እንመለከታለን ። ተልሚድን ደራሲው የአላማ ፅናትን ታማኝነትን ሰው እረጅነትን እንዲያንፀባርቅለት የመረጠው ገፀባህርይ ነው ።

3.2.3.5. የዝንመሪቅ አካላዊ አሰሳል

ዝንመሪቅ ጥቁር ግዙፍናቦርጫም መሆኑን ከመፅሐፉ ላይ እንደሚመለከተው አስፍሮታል ።

"ባለቤቱን ጥራልኝ" ዘበኛው በሩን መልሶ ጠረቀመው ። ከቆይታዎች በኋላ አንድ ፒጃማ ያጠለቀ ግዙፍ ሰው በሩን ከፍቶ ወጣ ።

"ማንን ፈልገህ ነው ?!" አለ ሰውየው የፒፓውን ጦስ በወፍራም ከናፍሮቹ መሀል እየተነለነለ።"( ገፅ፣114)

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ዝንመሪቅ ጥቁር እና ወፍራም  ፣ ቦርጫም ወፍራም ከናፍር ያለው አስፈሪ ገፅታ ያለው መሆኑ ነው ።

**3.2.3.6.የዝንመሪቅ ማህበራዊ አሰሳል**

ዝንመሪቅ ከዩኒቨርስቲ ተባሮ የቴክስታይል እንጅነሪንግ ትምህርቱን ያቋረጠና እስከ ግማሽ ድረስ የተማረ ነው።

ዝንመሪቅ ያገባ እና የአንድ ሴት ልጅ አባት ቢሆንም ከተለያዩ ሴቶች ጋር ፆታዊ ግንኙነት የሚያደርግ ከፍተኛ የሆነ የሀብት መጠን ያለው በስሙ "ዝንመሪቅ" የሚባል የግል ኩባንያ ያቋቋመ ነው ። ዝንመሪቅ ታዋቂ ኮንትሮባንድ ነጋዴ ነው ። የተለያዩ ልብሶችንና እቃዎችን ከተለያዩ ሀገራት በህገወጥ መንገድ ወደሀገሩ ያስገባል። ከዚህ ቀጥሎ ፀዳይ እና ብሩክታዊት ስለ ዝንመሪቅ ከተለያዩ ሴቶች ጋር እንደሚሄድ የተናገሩትን እንመለከታለን ።

"አባትሽ እንደሆነ በየሀገሩ ሚስቶች አበጅቷል አሉ። ቻይና ሀገር ሁለት አሜሪካ ሀገር ሶስት .....ሌላውን ትተን ከዚህች የደሃ ርምጦ የምታህለው ሀገር ከጅቡቲ አይቀር ሚስቶች አሉት አሉ። ልጆችም ሳያፈራ አይቀርም" (ገፅ፣34)

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ዝንመሪቅ በተለያዩ ምክንያቶች ከሀገር ሀገር እንደሚዘዋወር እና ብዙ ሚስቶች እንዳሉት ነው ።

### 3.2.3.7.ዝንመሪቅ ስነ-ልቦናዊ አሰሳል

"አንተ አጋሰስ አልበቃ ብሎህ እንጅ ያለን እኮ ይበቃን ነበር የሌሎችን መመኘት ማብቂያ አይኖረውም ?.....ግን ግን አይበቁህም እንደ ስለምን እቁባትህ ብዙ ናችው ምን ይበቃሀል። "አባት እንደለለው ልጅ" እንደሚባለው የንተ እዳ ሁሉ በልጀ ሳይሆን ሀጥያትህ ሁሉ ምንም በማይታወቀው አንዲቱ ፍሬየ ላይ ሆነ ።...."(ገፅ፣38)

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው የገንዘብ ምኞቱ ከፍተኛ እንደሆነ የሰውን ነገር መውሰድ የሚፈልግ ካለው በላይ ብዙ ሀብት እንዲኖረው የሚፈልግ ከገንዘብና ከራሱ ሌላ ማንንም የማይወድ ክብርና ዝና የሚወድ ገፀ-ባህሪ እንደሆነ ነው።

### 3.2.3.8. ዝንመሪቅ ሞራላዊ አሰሳል

ዝንመሪቅ ፍቅረ ንዋይ ያደረበት ስግብግብ ከሰው ይልቅ ገንዘብ የሚያስቀድም በተንኮልና በሴራ የተጠመደ ነው ። ስለ ዝንመሪቅ ከመፅሀፉ ላይ ለመግለፅ እየተፈለገውን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

"አባትሽ ላንች ደስታ የለውም የሚጨነቅልሽ እንዳይመስልሽ ። እሱ እንደ ባንዳ ኮንትሮባንድ እቃ ከሚጠፋበት አንችንና እንኔ ቢያጣ ይመርጣል። "(ገፅ፣ 39) ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ዝንመሪቅ ከሰው ይልቅ ቁሳዊ ሀብቶቹን እንደሚያስቀድም ገንዘብ በቃኝ የማይል ስግብግብ መሆኑን ነው ።

"በእርግጥ ዝንመሪቅ ማንም ሰው አይሆንም "አይሆንም ፣አይችልም የለም ....." ብሎ ሲናገር ተሰምቶ አይታዎቅም ጠላቱም ቢሆን ። " ልክ ነህ ትክክል ነህ " ማለት ልማዱ ነው ። ውስጥ ውስጡን ግን የዚህ ተቃራኒ ነው ። እረግብ ሆኖ የመጣውን ጠላቱን እባብ ሆኖ ሲጠመጠምበት አፍታ አይፈጅም ። አስቸጋሪው ነገር እባብ ሆኖ እስኪናደፍ ደስታ አለመሰማቱ ነው። ከነመፈጠሩም ገዳይ መርዙ በጠላቱ ደሞ ውስጥ ቀስ በቀስ እስኪሰራጭ አይታዎቀውም እነዚህን ጠባዩን እያፈራረቀ ይጠቀምባቸዋል። ሆኖም ስተት ከሰራ በኋላ ለሰው ቀርቶ ለራሱም ምህረት የሚደረግ አይመስለውም "(ገፅ ፣18)

ከዙህ ገለፃ እንደምንረዳው ዝንመሪቅብልጥ አስመሳይ በቀለኛ ጨካኝ ውለታ የሚባል ነገር የማያውቅ ነው።

"ዝንመሪቅን ለጥቂት ባለስልጣናትና እጅግ ጥቂት ከሆኑ ባለሀብቶች በቀር ማንም አያውቀውም። ዝንመሪቅ ተብሎ ይጠራ እንጅ ጨካኝ እና አረመኔ በቀለኛነቱም "ጊንጥ"የሚል ቅፅል ስም የወጣለት ገፀባህርይ ነው ።

ከዚህ ልቦለድ ውስጥ ደራሲው ማስተላለፍ የፈለገው እኩይ ባህሪያትን ጨካኝነትን ብልጥነትን ስግብግብነትን ውለትታ አለማዎቅን ሁሉ እንዲገልፅ አድርጎ የሳለው ገፀ-ባህሪይ ነው ።

### 3.2.3.9. የፀዳይ አካላዊ አሰሳል

ፀዳይ በ20ዎች እድሜ ክልል የምትገኝ እንደ አበባ የምትስብ ቆንጆ ይህ ቀረሽ የማትባል ሁሉን አሟልቶ የሰጣት ናት ። ስለፀዳይ ቁንጅና እናቷ መፃህፉ ላይ የገለፀችውን እንመልከት ።

"በሳቋ ውስጥ የሚፈልቀው ውበት እግዚአብሔር ጥርሶቿን ለመፍጠር ያማከረው ጠቢብ እና የፈጀበት ቀን ብዛት በዚች የጥዋት ጀምበር ጨረርከወትሮው ልቆ ይታያት ነበር። በልኳ ለሷ ብቻ የተፈጠረ የሚመስለው አፍንጫዋ ጥግ እና ጥግ እንደ ጦር የሚዋጉት አይኖቿን በጥልቀት እንዳፈቀረ ጎረምሳ እየተመለከተች ፣"

"ቆንጆ እኮ ነሽ ልጅ !....እንኳንስ ወንድ ሴትን የሚያስደነግጥ ውበት ታድለሻል እኮ ።" (ገፅ፣34)

ከዚህ ንግግር ብሩክታዊት የፀዳይን ውቀት ወደር እንደሌለው ለማስተዋወቅ ሞክራለች ።

### 3.2.3.10.የፀዳይ ማህበራዊ አሰሳል

ፀዳይ ዝንመሪቅ እና የብሩክታዊት ብቸኛ ልጅ ስትሆን ያላገባች እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋ እና ስነፅሁፍ ድግሪ ያላት "መርደራ" በሚባል በሽታ ተይዛ ሞቷን የምትጠባበቅ ናት ። ፀዳይ ከተልሚድ ጋር በደረገችው ንግግር ስለ ፍቅር ህይወቷ እና እና ስለትምህርት ሁኔታዋ ትገልፃለች ።

"እጮኛ የለኝም ። ድሮ ነበረኝ ተለያይተናል ።"

"እዚህ ከተማ ውስጥ የሚኖር ሰው ነው ?"

"ነው ግን አሁን አግብቶ ወልዷል ። የቤተሰቦቸን ሀብት ፍለጋ ነበር የተጠጋኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስነፅሁፍ እያጠናሁ በነበረበት ወቅት ነው ይሄ የሆነው ። በመጀመሪያ ድግሪ ስመረቅ አበባና ቀለበት ይዞ መጣ ።በጀሮየም በቅርቡ ሊያገባኝ እንደሚፈልግ ነገረኝ ።" (ገፅ፣63)

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ፀዳይ ያላገባችና በስነፅሁፍ ድግሪ ያላት መሆኗን ይገልፃል።

### 3.2.3.11. የፀዳይ ስነ-ልቦናዊ አሰሳል

ፀዳይ እናቷን አብዝታ የምትወድ አባቷን በሚሰራው ተንኮል የምትጠላ በተልሚድ ፍቅር የተያዘች ሰውን ማገዝ መርዳት የምተዎድ ተልሚድ እጁን በመቆረጡ ተስፋ ቆርጦ አልፅፍም ባለበት ሰዓት ከጎኑ ሁና እየረዳችው በግራ እጁ መፃፍ እንዲለመማድ ስታደርገው እንመለከታለን ።(ገፅ፣119)ፀዳይ አባቷን እንዴት እንደምትጠላው የሚከተለውን ንግግሯን እንመለከታለን ።

"የኔ አባት ማለት እኮ ይሁዳ እየሱስን በሰላሳ ዲናር እንደሸጠው ስታናግረው ....."ደግ አደረገ ግን ያዋጣዋል ? .....እኔ ይሁዳን ብሆን ኖሮ እየሱስን በሰለሳ ዲናር አልሸጠውም ነበር ።.....መጋዝን ውስጥ አስገብቸ ዋጋው እንዲንር አድርጌ ነበር የምሸጠው ።" የሚል ስግብግብ አባት ነው ያለኝ። "(ገፅ፣137)

በዚህ ንግግርም ፀዳይ የአባቷን ስግብግብነት እንደምትጠላው የገለፀችበት ሲሆን ፀዳይ አባቷን እንደምትጠላው የገለፀችበትን ሌላኛውን ንግግሯን ቀጥለን እንመልከት።

"አባትሽ ቀለል ሰው የመስልሻል ?"

"አባትሽ አትበይ ! ያንን ጨካኝ ያንን አረመኔ እ...እናቴ እኮ ለኔ አስታማሚየ ፀዳይ ትንፋሿን ውጣ እንባዋን ዘረገፈችው ።"(ገፅ፣148)

በዚህ ንግግሯ ፀዳይ ለእናቷ ያላ

ፃፍ ሲጀምር ማየት እና እናቷን ድጋሜ ማየት የምትፈልግ ገፀባህርይ ናት ።

### 3.2.3.12. የፀደይ ሞራላዊ አሰሳል

ፀዳይ በጣም አስተዋይ ቅን ልብ ያላት ነገሮችን ለመፍታት የምትሞክር ክብር የምትፈልግ እሂንም ከተልሚድ ጋር ባደረገችው ንግግር ለመግለፅ ተሞክሯል ።

"ፀዳይ በቀጫጭን ጣቶቿ የተልሚድን እንባ እየጠረገች ተጠጋችው"

"በክብር እንሞት እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ ።"

አዎ አንተ ብቻ በክብር እንድትገለኝ እፈልጋለሁ ። ይህን ብቻ ነው የማስቸግርህ ...."(ገፅ፣159)

ከዚህ ንግግር መረዳት እንደምንችለው ፀዳይ ክብር የምትፈልግ መሆኗን ይገልፃል ።

### 3.2.3.13. ብሩክታዊት አካላዊ አሳሳል

ብሩክታዊት መካከለኛ ዉፍረት ያላት ቆንጆ በ 40ዎቹ የእድሜ ክልል የምትገኝ ገፀ- ባህሪ ናት።

### 3.2.3.14. የብሩክታዊት ማህበራዊ

ብሩክታዊት የዝንመሪቅ ህጋዊ ሚስት እና የፀደይ እናት በዙሪያዋ ባሉት ሰራተኞች ጥበቃወች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላት ስትሆን የተማረች እና የማስተርስ ዲግሪ ያላት መሆኗን ዝንመረቅ በተናገረዉ ንግግር እንመለከታለን

<< አንተ አረመኔ የእኔን እግረ እግረ ሙቅ ታስገባበት ? ምን እያደረክ እንደሆነ አዉቀኸዋል..? >>

<< እረ ባክሽ?!... የኔ ሊቅ የኔ ሊቀ ሊቃዉንት!.... በደናዉ ጊዜ ከማስተረስ ማስተርስ አማርጠሽ እንድትይዥ አደረኩ።... በእዉነቱ? ማንም ወንድ ሲያፈቅር አይኑን ጨፍኖ ነዉ። አይኑን የገለጠ እለት ግን የማንንም እርቃንነት አይቶ መቋቋም አይችልም። >> ከዚህ ንግግር የምንረዳዉ ብሩክታዊት የተማረች መሆኗን ነዉ (ገፅ ፣37) ብሩክታዊት <<ኢትዮጵያ ዉስጥ የምድር ባቡር ሰራተኛ ሆና መቀጠሯን ቀድሞ ነበር የሰማዉ በኮንትሮ ባንድ ንግድ ድልብ ባለሀብት የሆኑ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር የሞት ሽረት ትግል ታደርግ እንደነበር ነገር ግን ትግሉ የግሏ ብቻ በመሆኑ << የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ዉረር >>የሚለዉን << የአብረን እንብላ >> ፈሊጥ መቀላቀሏን ሰማ። ለዛዉም የደለበ ድብቅ ሀብት ያላት ሴት እንደሆነችም ታከለለት። >> (ገፅ ፣48) ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለዉ ብሩክታዊት የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ሰራተኛ እንደነበረች ሀብትም እንዳላት ነዉ ስለ ሀብቷ መጠንም ብሩክታዊት ከፀደይ ጋር ያደረገችዉን ንግግር እንመለከታለን።

<< ብሩክታዊት በአግራሞት በሁለት እጆቿ አፏን ይዛ። << ስሚኝ ልጄ... ያለሽኝ ብቸኛ ዘመድ አንቺ ነሽ። አንዲቷን ፍሬዬን እንዲህ በቀላሉ ማጣት አልፈልግም። አንቺ እንደ አሞሌ ጨዉ ስትሟሚ እያዬሁ እንዴት ዝም ማለት እችላለሁ? እንደምታይዉ አዱኛ ሞልቷል... ከመኪና መኪና አማርጠን ነዉ! ከቤት ቤት አማርጠን ነዉ! ከ... ኧረ ስንቱ !.....ታዲያ "እሱ " ሁሉን አሞልቶ አይሰጥ! ሀብቱን ሲያድለኝ ከፍሬዉ ነፈገኝ። >> (ገፅ ፣34) ከዚህ ሀሳብ የምንረዳዉ ብሩክታዊት በጣም ሀብታም መሆኗን ግን ከአጠገቧ እናት አባት ዘመድ የሚባል ነገር እንደሌላት ይገልፃል።

### 3.2.3.15. የብሩክታዊ ስነ-ልቦናዊ አሳሳል

ብሩክታዊት ልጇን በጣም የምትወድ ለእሷ ብላ ከባሏ እስከ መፋታት ብሎም እራሷን ከአዳጋ የምትጥል ገፀ - ባህሪ ናት። ቅን ልብ ያላት ልጇን መዳር ፍቅረኛ እንድትይዝ የምትመኝ በባሏ በዝንመሪቅ የምትናደድ ናት። ብሩክታዊት ከፀዲ ጋር የምታደርገዉ ንግግር ልጇ በህይወት እንድትቆይላት እና ፍቅርኛ እንዲትይዝ የምትለምንበትን ቃለ ምልልስ ቀጥለን እንመለከታለን። << ምነዉ ልጄ በጭንቀት ባልሞትብሽ... ምነ ግልፅ ብትሆኝልኝ ልጄ... እኔ እኮ ካንቺ በቀር ማንም የለኝም።... እ? እናቴ ሆዴ? ለምን ትሸሸኛለሽ? ጎደኛሽ ማለት ነኝ እኮ.... እ? አንቺ እኮ እህቴም ፣ ልጄም ፣ጓደኛዬም ሁሉንም እኮ ነሽ... ማነዉ እኔን መሸሽ ያስተማረሽ

<< ... ም..ምን አድርጊ ነዉ የምትይኝ?... >>

<< ለዛ ለከርታታ ችግርሽን ነግረሽዋል? >>

<< ብነግረዉስ?! ምን ሊፈይድ ይችላል? >>

<< ያንን ነገር ጀምራችሁዋል ? >>

ከዚህ ቃለ ምልልስ የምንረዳዉ ብሩክታዊት የልጇ ህመም በጣም እንደሚያስጨንቃት ፤ብቸኝነቷ እንደሚያሳስባት ልጇ ከተልሚድ ጋር የፍቅር ግንኙነት እንዲኖራት እንደምትፈልግ ለመግለፅ ተሞክሯል።

### 3.2.3.16. የብሩክታዊት ሞራላዊ አሳሳል

ብሩክ ለሰዉ የምትራራ እና የምታዝን እንዲሁም ሰዉ የምታከብር መሆኑዋን የዝን መሪቅ የቤት ጥበቃ ሊያስተዋዉቅ ተሞክሯል።

<< ሌላ የሰማሁት የለም። ቁልፉን በአዲስ አስቀይሩ... ሔዱ። በቃ!

<< ሌላስ >>

<< መድሃኒዓለምን! የቁልቢዉ ገብርኤል ይቆማምጠኝ!። ሌላ የማዉቀዉ ነገር የለም። ባዉቅ በብሩክታዊት ልጨክን!?...እንኳንስ እኔ ....በእሷ ልጨክን ማን በሷ ይጨክናል! እንጀራዬ እኮ ናት... እሷ እኮ አጉራሼ.. እኮ ናት። እሷ እኮ የራቤ መድሃኒት ናት.. በሷ ብጨክን ቀኑም አይመሽልኝ። >>(ገፅ ፣102) ከዚህ ንግግር እንደምንረዳዉ ብሩክታዊት ደግ እና ለተራበ የምታበላ እሩህሩህ መሆኗን ነዉ።

### 3.2.3.17. የዝንመሪቅ ጥበቃ አካላዊ አሳሳል

የዝንመሪቅ አካሉ የደከመ ድምፁ የሰለለ በ 60ዎቹ እድሜ ዉስጥ የሚገኝ ገፀ ባህሪ ነዉ ስለጥበቃዉም አካላዊ ሁናታ ከመፅሀፉ የተገለፀዉን እንመለከታለን።

<< ተልሚድ ወደዚህ ግቢ ከዘመናት በሗላ ስመለስ ግን እናቱን አላገኛቸዉም። ሲያንኳኳ ጣረሞት የመሰለ ዘበኛ በሩን ከፍቶ ማንን ይፈልግ እንደሆነ ይጠይቀዋል።>> (ገፅ ፣114) ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳዉ ጥበቃዉ አካላዊ ሁኔታዉ ደከም ያለ መሆኑን ነዉ

### 3.2.3.18. የዝንመሪቅ ጥበቃ ማህበራዊ አሳሳል

ጥበቃዉ ከዝን መሪቅ መኖርያ ቤት በጥበቃነት የሚሰራ እና ያላገባ መሆኑን መፅሐፉ ላይ እንደሚከተለዉ ተገልፃል።

<< ተሳስተዋል ጌታዬ!... ይህ የአቶ ተፈሪ ቤት ነዉ... የወይዘሮ ሰናይት ቤት አይደለም። >>ጣራሞት የሚመስለዉ ዘበኛ በሰለለ ድምፁ መለሰለት.. በሩን ጠረቀመዉ። >> (ገፅ 115 )

የዝንመሪቅ ጥበቃ ሥነ-ልቦናዊ

ጥበቃው አሰሪዎቹ ዝንመራቅን እና ብሩክታዊትን የሚወድ መሆኑን ስለ ብሩክታዊት ደግነት እና እርህራሄ ያወራበትን እንመለከታለን ።

"ሌላ የማውቀው ነገር የለም ። ባውቅ በብሩክታዊት ልጨክን!? ---------እንኳንስ --------እኔ በእሷ ልጨክን ማነው? እሷ ላይ ሚጨክን ------? እሷ እኮ እንጀራዬ ናት ------እሷ እኮ አጉራሼ እኮ ናት ። /ገፅ-102/ ለዚህ ንግግር ሊገለፅ የሞከረው ጥበቃው ብሩክታዊት እንደሚወዳት እና እንደሚያከብራት ነው።

### 3.2.3.19. የዝንመራቅ ጥበቃ ሞራላዊ አሳሳል

ጥበቃው ለጌታው እና ለእመቤቱ ታማኝ ቃሉን አክባሪ ከጌታው ትዛዝ ውጭ ምንም የማያደርግ እንደሆነ እና ከፀዲ ጋር እና ከተልሚድ ጋር በሚያደርገው ቃለ ምልልስ ለመግለፅ ሞክሯል ።

" ሳይከፍት ደቂቃዎች ካለፉ በሀላ የሚያባባ የሚመስል ድምፅ ከውስጥ ይሰማቸዋል ።

" ማ ------ማማ ---ማን ልበል! " በተደናገጠ ድምፅ ነበር ።

" እኔ ነኝ ዝም ብለክ ክፈት! "

" አልከፍትም አንቺ ማነሽ "

" ፀአዳ ነኝ ዝም ብለክ ክፈት "

" ለማንም እንዳልከፍት ጋሼ አዘውኛል "

"እንዴ! አንተ! እኔ እኮ ፀ ------"

" እኔ ደጅኔ ካልሆኑበቀር ለፀአዳም ቢሆን ፣ ለማንም ቢሆን ፈጣሪ እንኳን ቢያንኳ እንዳትከፍት ብለውኛል ። ከዚህ ንግግር የምንረዳው ጥበቃው ታዛዥ እና ታማኝ መሆኑን ነው ። የዝንመራቅ ጠባቂ ፈሪ እንደሆነ ለመግለፅም ተሞክሯል ።

" እጆችክን ግንዱ ላይ አሳርፍ! "

" ኧ?! ለምን!? ------ኧ ----ኧ ----ል -----ልትቆርጠኝ ነው?! ------ምን አጠፋው የኔ ጌታ? ምም ---- አጠፍው ------"

"እጆችክን ግንዱ ላይ እሰረው አለበለዝያ አናትህን አገምሰዋለው -----"

" ኧረ -----ኧረ! ----- ኧረ የሰው ያለህ "(ገፅ101) ከዚህም ንግግር ፈሪ እና የሚርበተበት መሆኑ ተገልፆል።

### 3.2.3.20. የብጡል አካላዊ አሳሳል

ብጡል ሲለብስ የሚያምርበት ግርማ ሞገስ ያለው እድሜው ከ50ዎቹ መጀመርያ ላይ ያለ ሰው ነው ። ስለብጡል አለባበስ ከመፃፍ ለመውሰድ የተሞከረውን ስንመለከት ።

" ጓደኛዬ ላንተ ብዬ እንጅነር ብጡል መቃብሩን ፈንቅሎ እንዲወጣ አድርጌዋለው ። ብሎ በሩን ሲበረግደው ብጡል ቀይ ሱፍ የለበሰ እየሳቀ ጥልቅ አለ! " ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው ብጡል ሙሉ ሱፍ እንደሚለብስ ነው ። (ገፅ:89)

### 3.2.3.21. የብጡል ማህበራዊ አሳሳል

ብጡል እንጅነር እናየቴክ ስታይል እንጅነሪግ አስተማሪ ነው ። ብጡል የብሩክታዊት ታላቅ ወንድም ነው ። ስለ ቴክስታይል አስተማሪነቱ ገለፃ እንደሚከተለው እንመለከታለን ።

"ቻይና ውስጥ ከብዙ አመታት በፊት ሲገናኙ ዝንመረቅ ከዩኒቨርሲቲ ተባሮ የቴክስታይል አስተማሪ ሆኖ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያየውን አንድ ሀበሻ እንደጓ ደኛ ቆጥሮ ያስጠጋዋል እንጅነር ብጡል ።(ገፅ 47) ይህ ገለፃ የሚያመለክተው ብጡል በቻይና ውስጥ የቴክስታይል አስተማሪ እንደሆነ እና የዝንመራቅ ጓደኛ እና የረዳው ሰው እንደሆነ ነው ።

### 3.2.3.22. የብጡል ስነ -ልቦናዊ አሳሳል

"ከበአድ ሀገር ባርነቴ አከተመ! " (ገፅ 107) ብጡል ከስደት እና ከበአድ ሀገር ነፃ መውጣት የሚፈልግ መሆኑ የተገለፀበት ነው ። ሀገሩን የሚወድ እና እህቱን የሚወድ ነው ። ከዝንመረቅ ጋር ባደረገው ንግግር ለገሩን እንደሚወድ ተገልፆል ።

" ዋናው ጥይት መከላከሉ ነው ። እኔ ሌላው ጉዳይ አያገባኝም ። ኤም ኤስ ኤስ ከፈለገ የመሪዎች ፈስ ሁሉ ያዳምጥበት "

" አንተ! ምን አይነት ፈዘኛ ሰው ነክ ባክህ! ይህ እኮ አፍሪካን እንደገና ለመቀራመት የተላከ እጅግ ዘመናዊ ጆሮ ነው ። ለብዝበዛ ፣ ለዝርፊያ ፣ ----" ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ብጡል ለሀገሩ መልካም ነገር እንደሚመኝ ነው ።

### 3.2.3.23. የብጡል ሞራላዊ አሳሳል

ብጡል ደግ እና ሰው የሚረዳ መሆኑን ዝንመራቅ ከዩኒቨርሲቲ ሲባረር አስጠግቶ ያኖረው እንደነበር የተገለፀውን እንመልከት ።

"ከብዙ ዓመት በፊት ቻና ውስጥ ስገናኙ ዝንመርቅ ከዩንቨርስት ተባሮ የቴክስታይል እንጅነሪግ ትምርቱን አቋርጦ ነበር። ያኔ የ ቴክስታይል እንጂነሪንግ አስተማሪ ሆኖ የዩኒቨርስቲ ውስጥ አንድ ሀበሻ እንደ ጌደኛው ቆጥሮ ያስጠጋል....እንጂነር ብጡል። ከ እሱ ቤት ተጠግቶ ሲኖር ነበር ዝንመሪቅብሩክታዊትን የተዋወቃት።" (ገጽ፣47) ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው ብጡል ስው መርዳት የሚወድ መሆኑን ነው።

### 3.2.3.24. የወይዘሮ ስናይት አካላዊ አሳሳል

ወይዘሮ ስናይት እንደማያቸው ከ ስባ በላይ የሆኑ ፅጉራቸውን አፋሮ የሚያበጥሩ አሮጊት መሆናቸውን የምገልፅ ንግግራቸውን ቀጥለን እንመለከታለን ። "መርካቶ። በዚህ ግርግር ውስጥ አንዲት አሮጊት በመርቲ ጣሳ በርበሬ ሞልተው ወደ ጦር ግንባር ለመሄድ ከ ቦሌ 19 ቀበሌ ተነስተው መጡ ። ይፎክራሉ፣ ይሸልላሉ....ፅጉራቸውን እንደ እናት አርበኛ አበጥረዋል።"(ገፅ፣118)

### 3.2.3.25. የወይዘሮ ስናይት ማህብራዊ አሳሳል

"ባለቤቴ ሶማሊያ ጦርነት ወድቁዋል፤ልጁዋም ሀገሩን አገልግሉዋል።" (ገፅ፣118) ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ውይዘሮ ስናይት ባላቸው የሞቱባቸው እና አንድ ልጅ ያላቸው መሆኑን ነው። ወይዘሮ

ስናይት በ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ይኖሩ ነበር እና ማንበብ እና መፃፍ የማይችሉ መሆናቸውን በሚከተለው ገለፃ እንመለከታለን። “ቤቱን ከ ሸጡልኝ በሁዋላ ግንዘቡን አጠፋፍተው ቢቸገሩ ጊዜ እዚሁ ግቢ ውስጥ አንዲት ክፍል ቤት ሰጥቻቸው በነፃ ይኖሩ ነበር። ግባ!"

"ከዚች ቤት ነበር እናትህ ይኖሩ የነበር።" ሳንቃዋን ከፍቶ ወደ ውስጥ ጋበዘው።

"ከጥግ በኩል አንድ ሲቀመጡበት የሚቀባጥር አሮጌ አልጋ ፣ከጥጉ ደግሞ አሮጌ ሳጥን፣ከምድጃው ጥግም አመድ የቃመ ድስት ...ሌላ ደግሞ አንድ አሮጌ መሶብ እና አንድ ሌላ የተጨማደደ ሌማት። ልላው እቃ ከ አይን አይግባም። "(ግፅ፣ገ6) ከዚህ ገለፃ ለመግለፅ እንደተሞከረው ወይዘሮ ስናይት ብ ድህነት ይኖሩ እንደነበር ነው።

"ታድያ እናቴ ወዴት ሄደች?....እኔ ልፃፍኩት ደብዳቤ ለምን እስከዛሬ አልመለስችልኝም?"

"ማንበብ እንደ ማይችሉ ታውቅ የለ?"

" ታዲያ የ ሚያነብላት አጣች?" ከዚህ ቃለ ምልልስ የምንረዳው ወይዘሮ ስናይት ማንበብ እና መፃፍ እንደማይችሉ ወይም እንዳልተማሩ ነው።

### 3.2.3.26. የወይዘሮ ስናይት ስነ-ልቦናዊ አሳሳል

ወይዘሮ ስናይት ልጃቸው ተልሚድን የሚወዱ፣ሀገራቸውን የሚወዱ ጭፈራ እና ዘፍን የሚወዱ መሆናቸውን ከሚከተለው ግለፃ እንመለከታለን።

"የወዶ ዘማች ሀሞት ለማቆምጠጥ ከ ምዘፈነው ዘፈን ጣሳቸውን ሀረቄ እንደ ሚሸልም ሰው ከፍ አድርገው ገብተው የ ጥንቱን እስክታ ያስነኩት ጀመር። ዘፈን ሲያወጡ አዳሜ እጁ እስኪሞሸለቅ አጨብጭቦ።"(ገፅ፣ ገ8)

### 3.2.3.27. የወይዘሮ ስናይት ሞራላዊ አሳሳል

"ባለቤቴ በ ሶማሊያ ጦርነት ወድቋል፤ልጁዋም ለ ሀግሩ ዘምቱዋል። አሁን የማዘምተው ወግን የለኝም። እኔ ይህቺን በርበሬ ይዤ ለመዝመት ነው አመጣጤ ..... የደጀኑን ጦር ለማገዝ ... ይህቺ በርበሬ አትናቅም፤ ቢያንስ ለ አንድ ጎላ ወጥ ታግለግላለች።"(ገፅ፣ገ9)

ከዚህ ንግግር እንደምንረዳው ወይዘሮ ስናይት ጀግና የማትፈራ የሰዉን ወኔ የምትቀስቅስ ያላትን የምትስጥ ደግ የማትሰስት መሆኑዋ ነው።

### 3.2.4 " የተልሚድ" ረጅም ልብ-ወለድ ግጭት

የተልሚድ ረጅም ልብ-ወለድ በምእራፍ ሁለት ከተመለከትናቸው የ ግጭት አይነት ሁለቱን ማለትም ሰው ከ ሰው የምያደርገውን ግጭት እና ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የሚያደርገውን ግጭት ተጠቅሙዋል ።ሰው ከሰው ጋር በሚያደርገው ግጭት ብሩክታዊት እና ዝንመሪቅ የ ሚያደርጉትን ግጭት ስንመለከት ብሩክታዊትን ዝንመሪቅ ያለውን ንብረት በ ፍቺ እንድትካፈለው የውሸት ያአበደች አስመስሎ አማኑኤል የ አእምሮህሙማን ሲያስግባት የተመላለሱትን ቃለ ምልልስ እንደማስረጃ ቀጥሎ እንመለከታለን።

"እጅዋን ከወንበሩ ጋር የፊጥኝ ጠርቆ አሰረው። ሰፊ ጥቁር ፕላስተር አውጥቶ አፏን ሊሸብብበት ሲል እልህ በተናነቀዉ ድምፅት " እ...እኔ....እግር ላይ ሰንሰለት?!"....ስትል በደመ ነፍስ ጮኸች ብሩክታዊት። ምን ልታደርገኝ ነው?!"

" ማንም ቀድሞኝ አያውቅም!"

" አንተ አረሜ! የእኔን እግር.....እግር ፤ ሙቅ ታስግባለክ?"

" አላርፍ ላለ እግር እግረ ሙቅ መቼይበቃዋል ብለሽ ነው! መቁረጥ እንኩዋ ሲያንሰው ነው።"

" ምን እያደረክ እንደሆነ አውቀህዋል.....?"

"ከ አጥቂወቼ ጋር የተሰለፈ ሁሉ ላቅ ባለ መንገድ ይጠቃል...ይቀጣልም!"(ገፅ፣37)

ከዚህ ቃለ ምልልስ የምንረዳው ዝንመሪቅ ብሩክታዝዊትን በፍቺ ያለውን ሀብት እንድትካፈለው ለማድረግ ወደ ፈጠረላት ወጥመድ እና ሴራ ሲያስግባት የተነጋገሩት ቃለ ምልልስ ነው። ብሩክታዊት ልጇዋን ለማስታመም በቂ ገንዘብ ስላላገኘች እና ዝንመሪቅም ለ ልጇ ትኩረት ስላልሰጣት ከሱ ጋር ተፋታ የ ሚደርሳትን ይዛ ልጅዋን ማስታመም ሲሆን ፍላጐቱዋ፤ የዝንመሪቅ ደግሞያለውን ሀብት ላለማጣት እና በዚያ ላይ ለ መጨመር  ነው። በዚህም በ ም እራፍ ሁለት ሰው ከ ሰው ጋር የ ሚያደርግውን ግጭት አይነት ስንመለከት አንድ ሰው ምኞቱን እና ፍላጐቱን ለማሙዋላት ሲል የሚያደርገው ትግል የሌላኛውን ሰው ምኞት እና ፍላጐት  ሲጫን የሚፈጠር አለመግባባት ስለሆነ በ ዝንመሪቅ እና በ ብሩክታዊት

የተፈጠረው  አለመግባባት ሰው ከ ሰው ጋር የሚያደርገው የ ግጭት አይነት ዝንመሪቅ በ ማህበረሰቡ ዘንድ የ ተወገዘውን የ ኮንትሮባንድ ንግድ እናየ ሰዉን ህይወት ማጥፋት በ ማህረሰቡ የ ተጠላ እና በተንኮሉ"ጊንጥ" የሚል የቅፅል ስም እስከማውጣት የደረሱበትን ገለፃ ቀጥለን እንመለከታለን።

" ዝንመሪቅ እየተባለ በቅፅል ስሙ ይጠራ እንጂ እውነተኛ ማንነቱ ግን በአረመኔነቱ ጥቂቶች የሚያውቁት ተፈሪ ብለው ነው። ታዋቂው ኮንትሮባንዲስት። አንድአንዶች "ስኮርፒዮን" የሚል የሚስጥርስም አውጥተውለታል።"ጊንጥ" ብለው መሰየም ይችሉ ነበር፤ነገር ግን የተማሩ መሆናቸውን ለማሳበቅ ሳይሆን አይቀርም "ስኮርፒዮን" ይሉታል። ቢሆንም በለሆሳስ ካልሆነ በቀር"ስኮርብዮን"፣ "ዝንመሪቅ"  "ተፈሪብለው"፣ የሚሉ ስሞችን ድምፁን ዘለግ አድርጐ የሚጠራ ሰው የለም። "ስኮርፒዮን" እየተባለ መጠራቱን አያውቅም እንጂ ቢያውቅማ እንዲህ ብሎ ስም ያወጣለትን ሰው እንደ እሳት እራት ለማርመጥመጥ ደቂቃ ባልፈጀበት ነበር።"(ግፅ17)

ከዚህ ገለፃ የምንረዳው ዝንመሪቅ ብዙ ከማህበረሰቡ ጋር የሚያጋጨ ተግባራትን እንደሚፈፅም ነው። በ ምእራፍ ሁለት እንደተመለከትንው ደግሞ ከማህበረሰቡ ወግ እና ልማድ ውጭ የሆኑትን ድርጊቶች አንድ ሰው ቢፈፅም የሚጋጨው ግጭት ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የ ሚጋጨው ግጭት አይነት ነው።

" ለምን ተልመዲንን ጨርሳቹ አላጨዳቹትም? አ?  ያንን ዋግ የመታው እህልስ አራገፋቹት?"። ተወልደንስ ገደላችሁት? ማለቱ ነው። ያኛውን ደብረዘይት መውጫ ላይ አጭደንዋል። ተልሚድን ግን አልቻልንም፤ አሞልጧል። " ሶስት ግዜ አክሮባት በመስራት ነበር ወደ መንገዱ ዳር የወጣብን ። የመኪናው ጎማ ሊያገኘው የ ቻለው ከ አስፓልቱ ለ ጥቂት ለመውጣት የተፈናጠረበት ቀኝ እጁን ብቻ ነበር።" " በቃ! በቃ! ፅደይ ከወጣች በሁዋላ አንዳችሁ ገብታችሁ ጨርሱት። አንዳችም....አንዳችም ምልክት እንዳይገኝ። "(ገፅ፣27)።

ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው ዝንመሪቅ በማህበረሰቡ የተጠላውን እና የተወገዘውን የሰው ህይወት በማጣፋቱ ከማህበረሰቡጋር ያደረገውን ግጭት እና ተልሚድ ከዝንመሪቅ አገልጋዬች ጋር ያደረገውን አካላዊ ግጭት ወይም ሰው ከሰው የሚያደርገውን ግጭት ነው። የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ የዝንመሪቅ ገፀ-ባህርይ በሚፈጥራቸው እያንዳንዱ ሴራ ሰው ከሰው ጋር እና ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የሚያጋጭ ነው።

### 3.2.5. የ"ተልሚድ" ረጅም ልበ-ወለድ መቼት

#### 3.2.5.1. የ"ተልሚ"ረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ የቦታመቾት

የ"ተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ መቼት በዋነኝነት ኢትዬጲያ ቢሆንም ተልሚድ የተዘዋወረባቸው ሀገራት ግሪክ፣ማዳጋስካር እና ቻይናን ያጠቃለለ ነው።ለእምስረጅነትም ከመፃፉ የሚከተሉትን ገለፃወች እንመለከታለን።

"ተልሚድ ከስንት መንከራተት በሁዋላ በጅቡቲ በኩል አድርጎ ከስንት ድካም በሁላ ህይወት በራሷ አዙሪት ማዳጋስካር ድረስ አንገዋላ ወስዳው እንደነበር ትዝ አለው።በዚህም ሀገር በዋናው ከተማ በአንታና ናሪቮ አቅራቢያ ላለ እውቅ ባለሀብት ፣"ዜቦ"በመባል የሚታወቁትን ትልልቅ ሻኛ ያላቸውን አደገኛ በሬወችን ለማገድ ተቀጥሮ።በዚሁ በማዳጋስካር ሀገር በስው የሚጎተቱ ጋሪዎች ይጎትት ነበር።"(ገፅ፣ ፲፩)ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተልሚድ በማዳጋ ስካር ይኖር የነበረውን አጠቃላይ የቦታ መቸት ነው።

"ተልሚድ"ከማዳጋስካር ከወዛደርነቱ ወደ መርከብ

የፅዳት ሰራተኝነት ነት በመዘዋወሩ ከመርከቧ ጋር

ወደ ግሪክ ለመኮብለል የቻለው በዚሁ አጋጣሚ

ነው ።በታላቁ የአቴንስ ከተማ ኮሎኖኪ በሚባለው

የአቴንስ እምብርት በሆነው መንደር ውስጥ ለባለፅ

ጋዋ አንያን ተቀጥሮ ወሻ አጫዋች ሆኖ ነበር።፣"

( ገፅ፣12)ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው ግሪክ አጠቃላይ መቼት መሆኑዋን ነው።

ቻይና ቤጅንግ "በሻታንባክ"ጎዳና በሚገኘው "

ጆንግሻንደንግጂ"ሆቴል ውስጥ በመንፈላሰስ

ላይ ነው-ገጉንመሪቅ።"(ገፅ፣46)ከዚህ ግልጽ እንደምንረዳው ቻይና የተልሚድ ረጅም ልበወለድ አጠቃላይ መቼት መሆኗን ነው።

"አናንያ ተልሚድን "chapters of my life"በሚል

ዕርስ መፅሀፉን ሲጀምር ጥቂት ምዕራፎችን ብቻ

አንብባ በመስከሯ ነበ ድርሰቱ ምሉዕነት እንዲያገኝ

ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ኢትዬጲያ ተመልሶ እንዲ

ፅፍ ከብዙ ገንዘብ ጋር የሸኘችው ነው ኢትዬጲያ ለተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ መቼት መሆኑዋን ያስረዳል።

### 3.2.5.2"የተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድውስንየቦታ መቼት

በምዕራፉ ሁለት ላይ ለመመልከት እንደተሞከረው ውስን መቼት በአጠቃላይ መቼቱ ስር ሆኖ ታሪኩ የተፈፅመበትን ውስን የቦታ እና ውስን የጊዜ መቼትን ሲሄን የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ውስን የቦታ መቼት ለማስረጃነት ከመፅሐፉ ወስደን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

"በኮሎናኪ መንደር እናት ላይ በተኩፈሰው "ለካባትስ"በተሰኘው እውቅ ኮረብታ ስር በተንጣለ ግቢ ውስጥ ብቻዋን ያለባል ትኖራለች ቅብጥብጧአንያን። "(ገፅ፣12) ከዚህ ግልፃ ለመግለፅ የተሞከረው በግሪክ ሀገር ስላለ "ለካቤተስ"ኮረብታእና ስለ አናያና የተንጣለለ ግቢዋን ነው እሄም ቦታ በአጠቃላይ የቦታ መቼቱ ስር ሆኖ ታሪኩ የተፈፅመበትን ውስን የቦታ መቼቱን ይገልፃል።

"በማዳጋስካር በመርከብ ላይ ስር ወዛደርነት ተቀጥሮ ነበር።ወደ ግሪክ ለመኮብለል በለስ ሊቀናው ይችል ከኩሊነት ወደመርከቡ የፅዳት ሰራተኝነት በመዘዋወሩነው።"(ገፅ፣12)ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው በማዳጋስካር ውስጥ ተልሚድ

የመርከብ የፅዳት ሰራተኛ እንደነበር ነው።በተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ታሪክ ውስጥ መርከቧ ውስን የቧታ መቼትናት።

"አማኑኤል የአዕምሮ ለምን ሆስፒታል ከውጭ ስትይ ነጠላ ነው ግርማሞገስ የለውም።ለአይን የማይሞላ ጉጥባ ነው።ወደ የአዕምሮ ሆስፒታሉ በር ጠጋ ላሉ ገናከበሩ አስፈሪውን እና ዘግናኙን ጤነኛ እንኳ ን ቢሆን የሚያሳብደውን ትርዒቱን ይቋደሰል።"(ገፅ፣56) በዚህ ገለፃ ለመግለፅ የተሞከረው የአማኑኤል ሆስፒታል በአጠቃላይ መቼቱ ስር ሆኖ ብሩክታዊት አማኑኤል የገባችበትን ታሪክ የሚከናወንበት ውስን የቦታ መቼት መሆኑን ነው።

"ዝንመሪቅ ከቀዝቃዛው አየር ጋር ተቀላቅሎ" በሻታንባክ" ጎዳና እየተሸከረከረ ሲያስብ ቆይቶ ውድ ሆቴሉ ገብቷል።

በሰፊው የመኝታ ክፍል ውስጥ ካለው ምቹ ሶፋ ላይ ተቀምጦ ጥቅም ጣቱን እንደ ሽጉጥ ደግኖ ስለ ንግድ ሀሳቦች

ያወጣል ያወርዳል።"(ገፅ፣85)ይህ ገለፃ ዝንመሪቅ በቻይና ውስጥ በሻንታንጎዳና"ስላደረገው እንቅስቃሴ እናስለያዘው የመኝታ ክፍል የሚገልፅ የሚገልፅ ስህን በአጠቃላይየቦታ መቼቱ በቻይና ስር በ አረፈበት ሆቴል የተከናወኑትን ድርጊቶች ውስን የቦታ መቼት ይገልፃል።በተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ውስን የቦታ መቼት ኢትዬጲያ ውስጥ አማኑኤል ሆስፒታል፣የዝንመሪቅ የመኖሪያ ግቢ፣ቻይና ሻንግታንግ ጎዳናእና ዝንመሪቅ ያረፈበት ሆቴል፤በማዳጋስካር ተልሚድ የፅዳት ስር ይሰራበት የነበረው መርከብ፣በግሪክ "ነካቤተስ"ኮረብታእና የአንያን የተንጣለለ የመኖሪያ ግቢ ለተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ውስን የቦታ መቼቶች ናቼው።

### 3.2.5.3. "የተልሚድ"ረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ የጊዜ መቼት

የተልሚድረጅም ልበ-ወለድ አጠቃላይ የጊዜ መቸት ከ 1983 እስከ 1995 ዓ.ም ነው። ከመፅሃፉም ለአስረጅነት የሚከተለውን ገለፃ እንመልከት ።

"ይህም ወታደር ይህ ከሆነ ከስንት አመታት በሆላ ከሆስፒታል አልጋ ላይ ከሰመመኑ ሲነቃ የቀኝ እጁ

ተቆርጦ የነቃው ተልሚድ ነው። በጦርነቱ ላይ ተመቶ መሰለው። ነገር ግን ጦርነት ካበቃ ድፍን 12

አመት አልፏል ። አሁን 1983 ዓ.ም  አደለም ይልቅ 1995 ዓ.ም ነው። (ገፅ፡10)

ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው የተልሚድ ረጅም ልቦለድ ታሪክ ከ1983 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም የተከናወነ ስለሆነ የልቦለዱ አጠቃላይ መቸት ከ1983 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም ያለው ጊዜ ነው ።

### 3.2.5.4. "የተልሚድ" ረጅም ልበ-ወለድ ውስን የጊዜ መቸት

የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ውስን የጊዜ መቸት ቀናት ሳምንታት ወራትን ንጋትን ምሽትን የሚገልፅ ሲሆን ከመፃሀፉቱ ላይ የተጠቀሰውን የጊዜ መቸት ቀጥለን እንመለከታለን ።

"ያለወቅት በማልቀስ እውቅናን ያተረፈው የአዲስ አበባ ሰማይ በጠዋት እያለቀሰ በመሆኑ ለዝንመሪቅ መልካም እድል ነበር ። ሽቅብ የሚከተለውን መንገድ ሲከንፍ የአዲስ አበባ መንገዶች ሁሉ በሰማይ እንባ እንደዳከሩ ነበሩ  ወቅቱን ባልጠበቀ የመከር ወቅት ዝናብ። ምንም እንኳ ለዝንመሪቅ አስተማማኝ ሁኔታን ቢፈጥርለትም ለብዙዎቹ  የአዲስአበባ ወዛደሮች ግን አዲስ አበባ ውስጥ የሚዘንብ የክረምትም ሆነ የበጋ ዝናብ እንደ ዲያብሎስ ልጋግ  የሚያስጠፋ ይሆንባቸዋል ።"(ገፅ:39)

ከዚህ ገለፃ ከምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተመለከትነው የጊዜ መቸት ማጠቃለያቸውን የጊዜ ሁኔታዎች ማለትም ክረምት በጋ ጠዋት ምሽት የሚሉትን የጊዜ ሁኔታዎች የሚገልጽ ነው ።

### 3.2.5.5."የተልሚድ" ረጅም ልበ-ወለድ ማህበራዊ እውነታ

የተልሚድ ረጅም ልቦለድ ታሪክ የተከናዎነበት ቦታ የደርግ መንግስት

በኢህአዴግ ሰራዊት ተሸንፎ የደርግ ስርዓት ወድቆ የኢህአዴግ መንግስት ሀገሯን ለማስተዳደር የተረከቡበት ዘመን ነው። በዚህም ስለነበረው ጦርነት አስከፊ መሆኑን ኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እና የኤርትራ ተወላጆች በኢትዮጵያዊን ይደርስባቸው የነበርን መገለል እና ጦርነት በወቅቱ ስለተፈጠረው እረሀብ ለመግለጽ ተሞክሯል በዚህም ገለፃበዚህ የነበረው ማህበረሰቡ ሁኔታ በሚገባ ይገልፀዋል ፃል ።

" ግንቦት 1983 አረንጓዴ መሳይ ልብሱ የደርግ ወታደሮች አዲስአበባ ያልበሰለ ጎመን መሰለ ነበር ጦርነቱን ተሸንፈው  ተስፋ በቆረጡ ።አንገታቸውን መሳሪያቸውን በቀዝቀዝዚል ወታደሮች ተወረረች። ግማሹ በሽንፈታቸው ዳር ቁሞ ሲያላግጡባቸው የሳቅ ሳቅ ሲሳለቁባቸው ከአላጋጭ የተላከ ህፃን መቀመጫቸውን ከኋላ መጥቶ ቸብ አድርጎባቸ ሲሮጥ ማንም ምላሽ አይሰጡም ። አውራ እንደሌለው ያለመሪ የሚተሙት ወታደሮች ያፈርጣማ ክንዳቸው በሃፍረት ብብታቸው ውስጥ ገብቷል። ረሃቡም አድክሞቸዋል። "(ገፅ ፣10)

### 3.2.6. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ጭብጥ

አጥኝዋ የተልሚድን ረጅም ልበ-ወለድ አብይ አላማ ጭብጥ ብላ የወሰደችው ፅናትን ነው ። ተልሚድ ደራሲ የመሆን ህልሙን ለማሳካት ከማዳጋስካር እስከ ግሪክ ከዚያም ኢትዮጵያ እየተንከራተተ ነው። አላማውንም ለማሳካት ያለው ውጣውረድ የለም በሰው የማጎተቱ ጋራዎችን  እስከ ውሻ አጫዋች መሆን ድረስ ተሰቃይቷል ። እሄንንም የአላማ ፅናቱን ለማየት ከመፅሀፍ ማስረጃውን እንመለከታለን ።

"ተልሚድ ምንም ነገር የለውም ። ነገር ግን ሁሉም ነገር አለው። የሌለው ሊኖረው ሲል ያለው ያሙለጨለጨዋል። ያሙለጨለጨው ሲወድቅበት ደግሞ ሌላ አጓጊ እና የሚጨበጥ የሚመስል ጅረት ይመለከትና እጁን ይዘረጋል። ህይወት እራሷ እንደ አዙሪት እያንከራተተች እንደ እንደ እንዝርት እንቡልል እያሾረች ከሚፈልገው ሊደርስ ሲል ከማይፈልገው ስትዶለው ዘመኑን አጋምሰዋለች። እንደምንም ዘቅጦ ሊዎጣ ሲል ደግሞ እንደገና ሰርጅታ ከሌላ ጉድ ውስጥ ትደባልቀዋለች ። " (ገፅ፣9) ከዚህ ገለፃ ለመግለጽ የተሞከረው ተልሚድ ዓላማውን ለማሳካት ያለፈበትን ውጣውረድ እና ተስፋ አለመቁረጥ ነው የዚህ ልቦለድም ዋና ጭብጥ የአላማ ፅናት ነው። በውስጡም የተለያየ ንዑስ ጭብጥ ይዟል።

"ምን መሰለሽ ፀዲ ..... ደግነት እንጅ ፍቅር ያሳየሽኝ አልመሰለኝም ነበር ። .....ስለጥበብ አብረን የበድን ፣ በአፍቅሮተ ስነ-ፅሁፍ አብረን የነደድን መስሎኝ ነበር ....ለካ አንቺ አፍቅረሽኝ ስሜቴን ሳጎደጉደው ኑሬለሁ ።እንደ ቤቴን ስኮደኩደው ኑሬለሁ ። "(ገፅ-193)

ከዚህ ቃለምልልስ እንደምንረዳው የተልሚድ እና የፀዳይ ፍቅር የተልሚድ ረጅም ልቦለድ ንዑስ ጭብጥ መሆኑ ነው። ተልሚድ ረጅም ልቦለድ ውስጥ አንዳቸው ለአንዳቸው ብሩክታዊት ለወደፊቱ ያላት ፍቅር ፀዳይ ለተልሚድ እና ለእናቷ ያላት ፍቅር ደራሲው እንደ ንዑስ ጭብጥ ተጠቅሞታል።

"ዝንመሪቅ አማኑኤል የአእምሮ ህሙማንሆስፒታል ሲደርስ ማንም አልቀደመውም ነበር። ያለአንድ ርህራሄ

በሰው ሰወኛ ያላበደች የልጁን እናት ፣ የአእምሮ ህመማን መታከሚያ ወደተባለው አማኑኤል ሆስፒታል ወስዶ ዱሷት ተመለሰ።" (ገፅ ፣39)

ደራሲው በዚህ ገለፃ ለማንፀባረቅ የሞከረው የዝንመሪቅን ጭካኔ ነው።አጥኝውም በተልሚድ ረጅም ልቦለድ የተገለፀውን የዝንመሪቅ ጭካኔዎች እንደ ንዑስ ጭብጥ ወስዳ ተመልክታለች ።

"ብሩክታዊት ነገሩን ዳር አድርሳ ተፋታችው በሚሊዮን የሚቆጠር ሃብቱን ሊያጣ ሆነ። አብዳለች ብሎ ሆስፒታል ካስገባት ግን በጤነኛ አእምሮዋ አደለም ልፋታ ያለች ብሎ ፍርድ ወደ እሱ እንዲያጋድል ለማድረግ እንደሚችል ገምቷል። ከዚህ ባሻገር አማኑኤል ገብቶ ጤነኛ ሆኖ የሚወጣ አይኖርም ብሎ በማሰቡ ባለቤቴ በዚያው አብዳ እንደምትቀር ተስፋ አድርጓል ።(ገፅ ፣21)

ከዚህ ገለፃ እንደምንረዳው ዝንመሪቅ ገንዘብ ወዳድ ከሰው ይልቅ ገንዘብ የሚመርጥ ስግብግብ መሆኑን ነው ። አጥኝዋም ገንዘብ ወዳድነትን እንደሌላኛው ንዑስ ወስዳ ተመልክታለች።

### 3.2.7. የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ አንፃር

የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ የተጠቀመው አንፃር ሁሉን አዎቅ በመባል ይታወቃል ። ይህም የአንፃር ዓይነት በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተመለከትነው በልበ-ወለድ ውስጥ የሚከናወነውን ሁሉ የገፀባህሪያት ማንነት ፣እምነት፣አስተሳሰብ ፣አመለካከት ፣ስሜትና ፍላጎት በዝርዝር የሚያውቅ ነው። ገፀባህርይያትም ታሪክ የሚተርከው በሶስተኛ መደብ ነው እሱ፣እሷ፣እነሱ እያለ ሁሉንም የገፀባህሪያት ታሪክ አንድም ሳይቀር ለአንባቢያን የሚተርክ የአንፃር አይነት ነው። የተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድም የእያንዳንዳቸውን ገፀባህርያት ታሪክ እሱ፣እነርሱ፣እሷ እያለ በተገቢው የታሪክ ፍሰት ይገልፃል። የተልሚድ ረጅም ልቦለድ የህይወት ታሪክ ከሁሉን አዎቅ አንፃር ተጠቅሞ እንደሚከተለው ይተርካል ።

ተልሚድ ሁሉን ነገር ለማስታዎስ ሲሞክር በአእምሮው ትውስታ ማህደር ውስጥ በውል ያልተሰደሩ ትዝታዎች ወውሽንፍር እንደ ቢራቢሮ የፀዳይ ወቅት ቅጠሎች ቅጥ ባጣ ወረራ እየከነፉ መጡለት ። እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል እንደነበር አስታዎሰ። ጦርነቱን ተሸንፈው ወታደሮቹ መሳሪያቸውን በእንጀራ ይለውጡ ጀመር። በዚህ መሀል ግን ጠመንጃ እና ጥይቱን በአሮጌ መፅሐፍ ቀይሮ "ለገሀር" ባቡር ጣቢያ ቀጣዩን ባቡር ተሳፍሮ ወደ ምስራቅ የገሰገሰ አንድ ወታደር ነበር ። በጅቡቲ በኩል ለማምለጥ ። ይህ ወታደር ይህ ከሆነ ከስንት አመታት በኋላ በሆስፒታል አልጋ ላይ ከሰመመኑ ሲነቃ ቀኝ እጁ ተቆርጦየነቃው ተልሚድ ነው ። ጦርነቱን ተሸንፈው ከተሰደዱት አንዱ ነው። በጅቡቲ አድርጎ ከስንት መንከራተት በኋላ ህይወት እራሷ አዙሪት ማዳጋስካር ድረስ አንጓላ ወስዳው እንደነበር ትዝ አለው። (ገፅ ፣ ፲፩)

በዚህም ገለፃ ተራኪው ተልሚድን ህሱ እያለ በህይወት ዙሪያ የተፈጠሩትን ታሪኮች አንድ ባንድ ሲተርክ የሚያሳይ ነው። የገፀባህሪቱን ታሪክ ሙሉ በሶስተኛ መደብ የሚተርክ የአንፃር አይነት በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ሁለንተናዊ አንፃር ነው።

# ምዕራፍ አራት

## 4.ማጠቃለያ እና የመፍትሄ

### 4.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥንታዊ ፅሑፍ አላማው በደራሲ ይሰማከ ወርቁየተደረሰውንተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ከረጅምልበ-ወለድ አላባውያን አንፃር ትንተና መስጠት ሲሆን በውስጡም ስለልበ-ወለድ ምንነት፣ስለ ልበ-ወለድ አላባውያን ምንነትእና የልበ-ወለድ አላባውያን በልበ-ወለዱ ውስጥ እንዴት እንደተገለፀመተንተን ሲሆንየተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ታሪኩ ሁሉንምአይነት ማህበረሰብ እየነካ የሚሄድ ሲሆን መቼቱምበሚገባ ተገልፃል።ማህበራዊ እውነታወችንጊዜውንእና ቦታውን ልማየት ታሪካዊ፣ መልካምድራዊእና ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን አግባብ በመጨመር ተደራሲያኑ መቼቱን በትክክል እንዲያውቁ እና እንዲረዱ አድርጓል።ገፀ-ባህርያቱን ስንመለከት አብዛኛውን ገፀ-ባህርያት ወጥ ተደርጉው ተስለዋል። ታሪኩ ውስጥ በዘላቂነት ይቀጥላሉ።ሁሉንም አይነት የአሳሳል አይነቶች ተስለው እና ተቀርፀው እናገኛቸዋለን።ሴራውን እና ግጭትን ስናይ ደግሞ በትክክል በተሰራበት ሴራ አማካኝነት ግጭቶች ጊዜውን ጠብቀው ይፈጠራሉ።ጭብጡንም ስንመለከት ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ ሁሉን አወቅ የአንፃር አይነት በመጠቀም የታሪኩን ቅደም ተከተልሳያዛባ ተገልፃል።በአጣቃላይ ተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ሁሉንም የልበ-ወለድ አላባውያን የተጠቀመ ሲሆን እያንዳንዳቸውን የልበ-ወለድ አላባውያን አጥኝዋ በመረጃ አስደግፋ በስፋት እና በጥልቀት ትተነትናልች።

## 4.2. የመፍትሄ ሐሳብ

ደራሲው በተልሚድ ረጅም ልበ-ወለድ ውስጥ ያሉትን ሰናይ ባህሪን የተላበሱትን ገፀ-ባህርያት ሁሉም ይሞታሉ ይታመማሉ ።መጨረሻቸውም እንደመልካምነታቸው ሳይሆን በአሳዛኝ መልኩ ያልቃል ። አጥኝዋም እንደመፍትሔ ደራሲው መጨረሻውን ሰናይ ገፀ-ባህርያት ስድስት እና ከገቡበት ችግር ሲወጡ እኩይ ገፀ-ባህርያት ደግም በተራቸው ሲቸገሩ ቢገልፅ እኩይ ነገር መጨረሻው እንደማያምር መልካምነት ደግሞ መልሶ እንደሚከፍል ቢያሳየን መልካም ነበር።

## ጥቅሶች በመግኛ ቋንቋቸው

1 the word literature is drives from the Latin word"litra"which means later of the alphapet or alphabetic litters.the word alphabet denotes the letters used in writing language. This shows that the derivation of the word suggests that general meaning of literature is closely connected with the practice of writing.

# ዋቢ መፅሐፍት


ብርሀኑ ገብረ-ፃዲቅ ።አጠቃላይ የአማረኛ ቋንቋ ።አዲስ አበባ፣በረከት ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፣ 2008ዓ.ም።

አለም እሸቱ።መሰረታዊየምርምርአፃፃፍዘዴ።አዲስ አበባ፣የቅድስተ ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋክልቲ ህትመት፣1994ዓ.ም።

ያለው እንዳወቀ።የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር።ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣2009 ዓ.ም።

ይስማከወርቁ።ተልሚድ።አዲስ አበባ፣ኤችዋይ ማተሚያ ቤት፣2005 ዓ.ም።

ዘሪሁንአስፋው።የስነፅሁፍመሰረታውያን።አዲስአበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣2005 ዓ.ም።

ፋንታሁን እንግዳ።ተውኔታዊመዝገበቃላትእናፍቾወቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ።አዲስአበባ፣ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1998አ.ም።

____።የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ።አዲስአበባ ፣አርትስቲክ ማተማያ ድርጅት፣2009ዓ.ም።

MATTHEWSB.FUNDAMENTALOF LITERATURE.ADDIS ABABA.ALPHA PRINTERS.2009.P.L.C.